# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



## ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተመደበዉ ሀብት ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


| አርዕስት | | ገጽ |
|---|---|---|
| | List of Abbreviations | iv |
| | ክፍል አንድ | |
| 1.1 | መግቢያ ------------------------------------------------ | 1 |
| | የምክር ቤቱ ዓላማ ------------------------------------------------ | 2 |
| | የጽ/ቤቱ ዓላማ ------------------------------------------------ | 2 |
| | የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር ------------------------------------------ | 2 |
| | የጽ/ቤቱ መዋቅርና የሰዉ ኃይል አደረጃጀት -------------------------- | 3 |
| | የፋይናንስ ምንጭ ------------------------------------------------ | 3 |
| | የኦዲቱ አላማ ------------------------------------------------ | 4 |
| | የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛዎች፣ ---------------------------- | 4 |
| | የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት ------------------------------------------------ | 5 |
| | የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ------------------------------------------------ | 5 |
| 1.2 | የሥራ ሂደት መግለጫ (Process description) -------------------------- - | 7 |
| | ክፍል ሁለት | |
| | ግኝቶች ------------------------------------------------ | |
| 2.1 | ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ፤መከላከልና ለመቆጣጠር የተገኘውን ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣ ------------------------------------------------ | 10 |
| | • ፈንድ በመስፈርቱ መሠረት የማይፈቀድና በወቅቱ የማይለቀቅ ስለመሆኑ፣ | 10 |
| | • አስፈጻሚ አካላት የተለቀቀላቸውን ፈንድ ከሀገር አቀፉ የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ (CCM) ፈቃድ ውጭ የሥራ ለውጥ (ሪፕሮግራም) የሚያደርጉ ስለመሆኑ፣ | 14 |

- ጽ/ቤቱ ፈንድ ለአስፈጻሚ አካላት ሲሰጥ የተሰጣቸውን ፈንድ የሚያወራርዱበት ጊዜ ተወስኖ በውሉ ላይ የማይቀመጥ ስለመሆኑ እና ቀድሞ የተሰጠ ሳይወራረድ ተጨማሪ ፈንድ ስለመለቀቁ፣ ------------------------------------- 16
- በኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት ስለሚፈልጉ ወገኖች ብዛት መጠን የተደረገ ጥናት ስለአለመኖሩ፣ ------------------------------------ 20
- የተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት (OIT) አቅርቦት የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ቫይረስ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ለሁሉምስለመዳረሱ፣ ----------------------------- 22
- ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎትን ስለማግኘታቸው፣ ------------------------------------------------- 23
- በፌዴራልም ሆነ በክልል የመረጃ አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና ልውውጥ ሥርዓት እንዲሁም የወጪ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርቶች ትክክለኛነት በተመለከተ ------ 25
- በየደረጃው የሚቀርቡ የአፈጻጸም ሪፖርቶችንና ሌሎች መረጃዎች ጥራና በወቅቱ ስለመቅረባቸው፣ ----------------------------------------------------------------- 28

2.2 በኤች·አይ·ቪ/ ኤድስ ዙሪያ የተገኘውን ፈንድ ለተፈቀዱት ተግባራት ብቻ መዋሉን የሚያረጋግጥ በቂ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥን በተመለከተ፣ ------------------------------------------------------------- 30

- የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈጻጸም በተመለከተ ------------------------------------ 30
- ለግንዛቤ ማስጨበጫ የተዘጋጁ መመሪያዎች ለመሰራጨታቸው ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ ---------------------------------------------------------------------- 33
- በክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች እና ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ አካላት መካከል ያለውን የተቀናጀ አሠራር ስለአለመኖሩ፣ 34
- የእቅድ እና የበጀት አፈጻጸም ላይ ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ስለአለመኖሩ፣ 35
- በየመ/ቤቶቹ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ሜይንስትሪሚንግ የማድረግ እንቅስቃሴን በተመለከተ ------------------------------------------------------ 36
- ሥልጠናዎችን በተመለከተ ተገቢው መረጃ ስለአለመያዙ፣ 38
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር አብረው ለሚኖሩ ዜጎች የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን በተመለከተ፣ --------------------------------------- 39

**ክፍል ሦስት፡**

3 መደምደሚያዎች ------------------------------------------ **41**

**ክፍል አራት፡**

4 የማሻሻያ ሀሳቦች -------------------------------------------- **44**

**አባሪ**

አባሪ 1 የኦዲት መስፈርት (Evaluative Criteria) ------------------ **48**

አባሪ 2 የሀገር አቀፉ የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ አባላት (Country Coordination Mechanism, CCM Members) ---------- **51**

# List of Abbreviations

| | |
|---|---|
| **ARV:** | **Anti Retroviral** |
| **CCM:** | **Country Coordinattion Mechanism** |
| **CDC:** | **Center for Disease Control** |
| **CIS:** | **Community Information System** |
| **CRIS:** | **Country Response Information System** |
| **EMSAP:** | **Ethiopia Multi-Sectoral AIDS Project** |
| **HMIS:** | **Health Management Information System** |
| **OIT:** | **Opportunistic Infectious Treatment** |
| **OVC:** | **Orphans and Vulnerable Children** |
| **SoE:** | **Statements of Expenditure** |
| **UNCEF:** | **United Nation Children Fund** |
| **UNDAF:** | **United Nation Development Assistance Framework** |
| **UNDP:** | **United Nation Development Program** |
| **UNFPA:** | **United Nation Population Fund** |
| **VCT:** | **Voluntary Counselling and Testing** |

# ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተመደበዉ ሀብት ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1 የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ መስፋፋት በመላ ህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሰውን ጫና በመገንዘብ እንቅስቃሴ የተጀመረው በአገሪቱ ውስጥ የቫይረሱ መኖር በላብራቶሪ ምርመራ ከመረጋገጡ በፊት ከ1978 ጀምሮ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት የተወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ውስጥ አንድ ብሔራዊ ግብረ ኃይል በ1977 ማቋቋም ነበር፡፡ ግብረ ኃይሉም በቅድሚያ ያተኮረው የችግሩን ሁኔታ በመተንተን አስፈላጊ የሆኑትን የሥራ መመሪያዎች በመንደፍና አቅም በመገንባት ላይ ነበር፡፡ በመቀጠልም የኤድስ መቆጣጠሪያ ኘሮግራም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ውስጥ በመምሪያ ደረጃ በ1978 ተቋቁሞ ብሔራዊ እንቅስቃሴውን ማስተባበር ቀጠለ፡፡ በዚሁ ወቅት የመጀመሪያው የአጭር ጊዜና ሁለተኛው የመካከለኛ ጊዜ ዕቅዶች ተነድፈው በሥራ ላይ ዋሉ፡፡

2 የብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት እና ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የሆነ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በሰኔ 1994 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 274/1994 ተቋቁሟል፡፡ የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከጥቅምት 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 471/1998 መሠረት እንዲዛወር ተደርጓል፡፡ በ1997 ዓ.ም. ብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፖሊሲ የወጣ ሲሆን፣ እርሱን መሰረት በማድረግም የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ማዕቀፍም ይፋ ተደርጓል፡፡

3 የብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት የሚመራ ሲሆን፣ የሚከተሉት አባላት አሉት፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የፌዴራል መንግስት ሚኒስትሮች፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የክልል ርዕሳነ መስተዳድር፣ የመገናኛ ተቋማት ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት መሪዎች፣ የሲቪክና የሙያ ማህበራት ኃላፊዎች፣ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት ተወካዮች፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ኃላፊና የስራ አመራር ቦርድ አባላት እና በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ታዋቂ ግለሰቦችን ያካትታል፡፡

## የምክር ቤቱ ዓላማ

4 የብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት አምስት ዓላማዎች ሲኖሩት እነርሱም:-

- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አግባብ ያላቸዉ አካላት ለችግሩ ይበልጥ ትኩረት ሰጥተዉ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግና የኅብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲያጎለብቱ በማበረታታት ጤናማ አመለካከትና ባህሪ የሚዳብርበትን ሁኔታ መቀየስ፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደረጉት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ጥረቶች በተናጠል ሳይሆን፣ በተቀናጀ መልክ እንዲካሄዱና ወጣቶችና ሴቶችን ጨምሮ ለበሽታው ይበልጥ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውን ከበሽታው ለመከላከል እንዲችሉ አስፈላጊውን እርዳታና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆች የጤና፣ የሥነ ልቡናና የምክር አገልግሎትና አስፈላጊውን የማቴሪያል ድጋፍ የሚያገኙበትን እንዲሁም ሰብዓዊ መብታቸው የሚከበርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የአገሪቱ የኤድስ ፖሊሲ ከአጠቃላይ የጤና ፖሊሲው ጋር ተቀናጅቶ ተግባር ላይ የሚውልበትን መንገድ ለመቀየስና የበሽታውን ሥርጭት ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ዕቅድና ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚረዱ ሃሳቦችን ማመንጨትና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የጥናትና የምርምር ተግባሮችን ማበረታታት፣
- በተጠናከረና በተቀናጀ መልክ ኘሮግራሞችን ለማስፈጸም ከአገር ውስጥና ከውጭ እርዳታ የሚሰባሰብበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

ናቸው፡፡

## የጽ/ቤቱ ዓላማ

5 የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት የተቋቋመለት አላማም የአገሪቱን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፖሊሲ አፈፃፀም ማስተባበርና መምራት ነው፡፡

## የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

6 ጽ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 274/1994 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥተውታል:-

- የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፣

- የምክር ቤቱን አስተያየት አካቶ የተዘጋጀ አገር አቀፍ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ኘሮግራም ለመንግስት አቅርቦ ያስጸድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ የፌደራልና የክልል መንግስታዊ አካላትንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
- ህብረተሰቡ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግንዛቤ እንዲኖረው አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ስብሰባዎችና አውደ ጥናቶች ያዘጋጃል፡፡ እንዲዘጋጁ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ስብሰባዎች ይሳተፋል፣
- በአገሪቱ ያለውን የገፅታ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናክራል እንደአስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሰራጫል፣
- ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፣
- በልገሳ የተገኘው ገንዘብና ከመንግሥት የሚመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ  ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡

## የጽ/ቤቱ መዋቅርና የሰዉ ኃይል አደረጃጀት

7 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በበላይነት የሚመራና የሚቆጣጠር የሥራ አመራር ቦርድ አለው፡፡ በቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የጽ/ቤቱን ሥራ በኃላፊነት የሚመራና የሚያስተዳድር ዋና ዳይሬክተር እና ም/ዋና ዳይሬክተር ሲኖረው፣ በስሩ አምስት ዳይሬክትረቶችና የህዝብ ግንኙነትና ኮምንኬሽን ክፍል ተደራጅቷል፡፡ ጽ/ቤቱ በአጠቃላይ 57 ቋሚ ሠራተኞች እንዲሁም 59 የኮንትራትና በሌላ መ/ቤት ደመወዛቸው የሚሸፈን 11 በድምሩ ወደ 127 ሠራተኞች በታህሳስ 30 2003 ላይ ነበሩት፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

8 ጽ/ቤት ተልዕኮውን ለማሳካት ከመንግስት፣ ከግሎባል ፈንድ እና ከአለም ባንክ እንዲሁም ከሌሎች ለጋሽ አካላት ማለትም እንደ ኡንዳፍ / [ዩኒሴፍ (UNCEF)፣ ዩኤን ኤፍ.ፒኤ. (UNFPA)፣ እና ዩ.ኤን.ዲ.ፒ. (UNDP) ጥምረት] የአሜሪካ የበሽታ መከላከል ማዕከል (CDC)፣ ኢ.ጋድ(IGAD)፣ ፑልድ ፈንድ (POOLed fund) የመሳሰሉት ፋይናንስ ያገኛል፡፡

9 ከግሎባል ፈንድ በሁለተኛ፣ በአራተኛና በሰባተኛ ዙር በዶላር 582,957,487፣ ከአለም ባንክ በሦስት ኮምፖነንት በዶላር 25,000,000፣ ከUNDAF ብር 9,972,002·60፣ ከCDC ብር

31,332,269·57፣ ከIGAD በዶላር 150,549·42፣ ከፑልድ ፈንድ (Pooled fund) ፓውንድ 1,500,000.00 ተመድቧል (ቃል ተግብቷል)፡፡

10 ከዚህ ውስጥ የተሰበሰበው ደግሞ ከግሎባል ፈንድ በሁለተኛ፣ በአራተኛና በሰባተኛ ዙር በዶላር 510,861,339·96፣ ከአለም ባንክ ከሦስት ኮምፖነንት በዶላር 18,183,717·00፣ ከUNDAF ብር 9,972,002·60፣ ከCDC ብር 31,332,269·57፣ ከIGAD በዶላር 150,549·42፣ ከPooled ፓውንድ 1,500,000.00 እና ከመንግሥት መደበኛ በጀት ብር 4,912,009·89 ከ1999 እስከ 2002 ዓም ባለው ጊዜ ወስጥ ተመድቧል፡፡ ጽ/ቤቱ የሚያገኘውን ገንዘብ በተዋረድ ለክልል እና ለሌሎች በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ለሚሰሩ አካላት ሁሉ በሚያቀርቡት የሥራ ዕቅድ ፕሮግራም መሰረት እያጣራ ገንዘቡን ያከፋፍላል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

11 የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር በአገሪቱ ውስጥ እየተስፋፋ የነበረውን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተገኘውን ሀብት፣ በታቀደለት ጊዜ፣ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የጽ/ቤቱ የመረጃ አያያዝ፣ ከአስፈፃሚ አካላት ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ ያለው ክትትልና ግምገማ ጠንካራ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ውጤቱ የሚፈለገውን ያህል ካልሆነ እንዳይሆን ያደረጉትን ችግሮች በመለየት በችግሮቹ ላይ የማሻሻያ ሃሳብ ለመስጠት ነው፡፡

### የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛዎች፣

12 ከላይ በተመረጠው የኦዲት አካባቢ ሥር ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit issues) ተመርጠዋል፤ እነርሱም:-

1.) ኤች·አይ·ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተገኘውን ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣
2.) በኤች·አይ·ቪ/ ኤድስ ዙሪያ የተገኘውን ፈንድ ለተፈቀደለት ተግባር ላይ ብቻ መዋሉንና በቂ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት

13 እነዚህን ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ኦዲት ለማድረግ 47 የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል። የመመዘኛ መስፈርቱም ለኦዲት ተደራጊዎች ተልኮ አስተያየታቸውን ሰጥተውበታል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

14 ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው። ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው በዋነኛነት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ሲሆን፣ ጥናቱንም ለማከናወን ከ2000 እስከ 2002 የበጀት ዓመት ድረስ የተከናወኑ ሥራዎችን የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስና፣ ለጽ/ቤቱ 4 ዳይሬክቶሬቶችና ለፕሮጀክትና ግራንት ማኔጅመንት ማስተባበሪያ የሥራ ኃላፊዎች፣ እንዲሁም ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ለመድሐኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ፣ ከግሎባል ፈንድ የኢትዮጵያ ወኪል ከሆኑ የሥራ ኃላፊዎች፣ እና የሚመለከታቸዉ የስራ ኃላፊዎችን በመጠየቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

15 በትግራይ፣ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ እና በጋምቤላ ሕዝቦች ክልሎችና እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች፣ የጤና ቢሮዎች፣ ለወረዳ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ. ዴስኮች ኃላፊዎች፣ በናሙና ለተመረጡ የጤና ተቋማት ኃላፊዎች፣ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ማህበራት ጥምረት ኃላፊዎች፣ ለእምነት ተቋማት የልማት ፎረም ኃላፊዎች፣ በናሙና ለተመረጡ የትምህርት ተቋማት ኃላፊዎች፣ ለሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፤ እንዲሁም ለሌሎች በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዙሪያ ለሚሰሩ የፌዴራል፣ የክልል መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አስፈጻሚ አካላት ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በመመርመር ነው። ነገር ግን ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ድረስ የጤና ጥበቃ ሚንስቴር፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 እና የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽ አልሰጡም፡፡

16 ከላይ እንደተመለከተው ኦዲቱን ለማድረግ ከተለያዩ መ/ቤቶች ማስረጃ መሰብሰቡ ተገልጿል፡፡ በዚህ መሰረት አንዳንድ በኦዲት ሪፖርቱ ውስጥ የተቀመጡ ግኝቶች፣ መደምደሚያዎችና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ጽ/ቤቱን ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆኑ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የተለያዩ በኤች.አይቪ./ኤድስ ዙሪያ ላይ የተሰማሩ የፌዴራል እና የክልል መንግስታዊ መ/ቤቶች እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን /አስፈጻሚ አካላትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለሁሉም መ/ቤቶች የሪፖርት ቅጂዎችን ለመላክ ከጊዜና ከአሰራር ግንኙነት አንጻር የተመቻቸ ባለመሆኑ፣ ጽ/ቤቱ በአዋጅ ከተጣለበት ኃላፊነት እና ከመ/ቤቶቹ ጋር ካለው የሥራ ግንኙነት ምክንያት ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሁሉ የሪፖርቱን መልዕክት እንዲያስተላልፍ እንጠይቃለን፡፡

## 1.2 የሥራ ሂደት መግለጫ (Process description)

### 17 ፩. ፈንድ ለማግኘት የሚደረግ ሂደት

ከአስፈጻሚ አካላት የፈንድ ፍላጎት ይቀርባል

↓

አስፈጻሚ አካለት መመሪያዉን ተከትለዉ ለፈንድ ጥሪዉ መወዳደር አለባቸዉ

↓

አስፈጻሚ አካለት የፈንድ ጥያቄያቸዉን/የስራ ዝርዝር መርሀ ግብር በማዘጋጀት ያመለክታሉ

↓

የሚመለከተዉ አካል ማብራሪያ ለፈለጉ አስፈጻሚ አካለት ማብራሪያ መስጠት አለባቸዉ

↓

አልፏል/ወድቋል

↓

ካለፈ ለቴክኒካል ሪቪዉ ፓናል ኮሚቴ/review technical panel committee/ይቀርባል

↓

የቀረበዉ  ዝርዝር የስራ መርሀ ግብር፣ ለፕሮጀክቱ የተፈቀደዉ ፈንድ እና ከተከለሰ በኋላ ስምምነት ላይ ይደረሳል

↓

ስምምነት የፈረማል

↓

ከለጋሾች ፈንድ እንዲለቀቅ ጥያቄ ይቀርባል

### 18 ፪. ለአስፈጻሚ አካላት ፈንድ የመፍቀድ ሥርዓት

ከለጋሾች ፈንድ ከተለቀቀ በኋላ

↓

ለአስፈጻሚ አካላት የፈንድ ጥያቄያቸዉን/ ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብራቸዉን እንዲያቀርቡ ጥሪ ይቀርባል

↓

በአስፈጻሚ አካለት የቀረበዉን የፈንድ ጥያቄ/ ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብር ይገመገማል፣ይለያል፣ይከለሳል፣ይጸድቃል

↓

የአስፈጻሚ አካላት የማስፈጸም አቅም ይፈተሻል

↓

ከአስፈጻሚ አካላት ጋር የዉል ስምምነት ይፈጸማል

↓

የግራንቱ ዉል ለስራ ሂደቱ ባለቤት /ለፋይናንስ/ ይሰጣል

↓

የተፈረመዉ የገንዘብ ስምምነት ዉል ለሂሳብ ባለሙያ ይደርሳል

↓

ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ መረጃዉ ይመዘገባል/የገንዘብ የማስተላለፊያ ደብዳቤ ይዘጋጃል

↓

የገንዘብ ማስተላለፊያዉ ደብዳቤ ይፈረማል

↓

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የገንዘብ ማስተላለፊያዉን ደብዳቤ በመዝገብ ቤት በኩል ወጪ ይደርጋል

⇩

የገንዘብ ማስተላለፊያ ደብዳቤዉን ለባንክ ይደርሳል

⇩

ለአስፈጻሚ አካላት በየምዕራፉ ፈንድ ይለቀቃል

⇩

ለአስፈጻሚ አካላት ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት የክትትል ስራ ይሰራል

⇩

ገንዘቡን ስራ ላይ አዉለዉ በጊዜዉ የአፈጻጸም  እና የወጪ መግለጫ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይደረጋል

⇩

ያቀረቡት ሪፖርት ትክክለኛነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል

⇩

ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ ሪፖርት በማቅረብ ለቀጣይ ፈንድ እንዲለቀቅላቸዉ ማመልከቻ ያስገባሉ

⇨ የቀረቡት ሪፖርቶች የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበቸዋል፣ የባህሪ ለዉጥ፣የአመለካከት ለዉጥና የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም የሚሰጠዉን አገልግሎት ጥራትና ሽፋን በማየት ለቀጣይ ፈንድ ይለቀቃል

⇩

የሂሳብ ማስተላለፍና የሂሳብ ማወራረጃ ሰነዶች ይደርሳሉ

⇩

የተላለፈዉ ፈንድ እና የተወራረደዉ ሂሳብ ተመዝግቦ ይቀናነሳል

⇩

ያልተወራረደዉን ሂሳብ በተመለከተ በስልክ ክትትል ይደረጋል

## *19 ፫. <u>የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ</u>*

የፋይናንስ ድጋፍ የተደረገላቸዉን ፕሮጀክቶች ፕሮፖዛል መርሃ ግብርና የስምምነት ሰነድ መቀበል

⇩

ፕሮጀክቶቹን/መርሃ ግብሮቹን የሚመለከቱ መሰረታዊ መረጃዎች መለየትና ማደራጀት

⇩

ፕሮጀክቶቹን መከታተል፣የአፈጻጸም ሪፖርት መቀበል መገምገም

⇩

በአካል ተገኝቶ ተጨማሪ መረጃ ማሰባሰብ

⇩

ከመነሻ እቅድ ጋር በማገናዘብ የግምገማ ሪፖርት ማቅረብ

⇩

የማጠቃለያና ኦዲት ሪፖርት መቀበልና ግብረ-መልስ በጽሁፍ መስጠት

⇩

## *20 ፬. የፈንድ ሂሳብ የማስተካት ሥርዓት*

ከፈጻሚ እና አስፈጻሚ አካላት የወጪ መግለጫ ሪፖርት ማሰባሰብ

⇓

ከፈጻሚ እና አስፈጻሚ አካላት የተሰበሰበዉን የወጪ መግለጫ ሪፖርት ማጠቃለያ መስራት

⇓

ከፈጻሚ እና አስፈጻሚ አካላት ተሰብስቦ የተጠቃለለዉን የወጪ መግለጫ ሪፖርት ለለጋሾች በማቅረብ ፈንድ ማስተካት

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## 2.1 ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ፣መከላከልና ለመቆጣጠር የተገኘውን ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት ዓላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣

### ፈንድ በመስፈርቱ መሠረት የማይፈቀድና በወቅቱ የማይለቀቅ ስለመሆኑ፣

21 ጽ/ቤቱ በኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ዙሪያ ፈንድ ለሚጠይቁ አካላት ፈንዱን ለመፍቀድ የሚረዳው መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ፣ በተቀመጠው መስፈርትና ጊዜ ገደብ መሰረት ፈንዱ ከተፈቀደላቸው አካላት ጋራ ውል ሊፈራረም ይገባዋል፡፡ ጽ/ቤቱ የሚፈራረመው ውል፣ በአስፈጻሚ አካላት ሥራው መቼ ተጀምሮ፣ መቼ እንደሚጨርሱት በግልጽ የሚያሳይ መሆን ያለበት እና ለዕቅድ ገምጋሚ ቦርድ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡ ውሉም ከተፈረመ በኋላ ፈንዱ በወቅቱ ሊለቀቅላቸው ይገባል፡፡ የክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ፈንዱን ለወረዳ፣ ለጤና ተቋማት እና ለሌሎች አስፈጻሚ አካላት ማስተላለፍ ይገባቸዋል፡፡

22 ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደተመለከትነው፣ በናሙና በተመረጡ አስፈጻሚ አካላት የቀረቡት ዕቅዶች በሀገር ደረጃ የተውጣጡ ባለሙያዎች በመመሪያ መሠረት የተቀመጠላቸውን የመከለሻ እና ማጽደቂያ ጊዜያቶች ተግባራዊ አላደረጉም፡፡ እንደዚሁም አስፈጻሚ አካላት የሚያቀርቡት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለማጽደቅ በሚደረገዉ ሂደት ላይ፣ በአገር ደረጃ የተውጣጡ የዕቅድ ገምጋሚ ባለሙያዎች ጋር ከመቅረባቸዉ በፊት፣ በቅድሚያ በመመሪያዉ መሰረት አስፈላጊዉ ሁሉ መሟላቱን የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ክፍል /ዩኒት/ ሳያረጋግጥ የሚቀርብ ሲሆን፣ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ገቢ ሲደረግም ገቢ የተደረገበት ቀን እና መለያ ቁጥር ተሰጥቶት ተመዝግቦ አልተገኘም፡፡

23 በኦዲቱ ወቅት፣ ከክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች ለ2001 በጀት አመት ዕቅዳቸውን ሳያቀርቡና በሪቪው ቦርድ ሳይታይ ከአለም ባንክ (EMSAP II) ብር 16,700,000.00 (አሥራ ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ብር) ተለቆላቸዋል፡፡ ለጤና

ጥበቃ ሚኒስቴር ለደም ባንክ ማቋቋሚያ ብር 38,958,002.00 (ሠላሳ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሀምሳ ስምንት ሺህ ሁለት ብር)፣ ለመድኃኒት ማከማቻ መጋዘን ግንባታ ብር 15,818,516.00 (አስራ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አስራ ስድስት ብር) እና ለጤና አስተዳደር መረጃ ሥርዓት (HMIS) ብር 26,6448,000.00 (ሃያ ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ብር) በድምሩ ብር 81,421,318 (ሰማንያ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሦስት መቶ አስራ ስምንት ብር)፣ ለ195 ጤና ተቋማት ግንባታና ማስፋፊያ የኮንትራት ዋጋ ሳይቀርብ የአሜሪካን ዶላር 35,735,553.00 (ሠላሳ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሠላሳ አምስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ሦስት የአሜሪካን ዶላር) ተፈቅዷል፡፡ ነገር ግን ገንዘቡ ሲጠየቅ፤ ስራዉ በየትኞቹ ክልሎች ምን ያህል ተቋማት እንደሚገነቡ፣ እንዲሁም የኮንትራት ዋጋቸዉን የሚያሳይ መረጃ ሳይኖር የተጠየቀው ገንዘብ ተለቋል፡፡

24 በተጨማሪም ለእነዚህ ተቋማት በተለቀቀው ገንዘብ ምን ያህል ተቋማት እንደተገነቡ፣ ተጀምረዉ ያልተጠናቀቁ ተቋማት ስንት እንደሆኑና ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ፣ እድሳት የተደረገባቸዉ ተቋማት ብዛት፣ የማስፋፊያ ስራ የተሰራባቸዉ ተቋማት እና የአዲስ ጤና ተቋማት ግንባታ ብዛት የሚያሳይ መረጃ ሳይቀርብ ቀሪዉን ስራው ለማጠናቀቅ ያስፈልጋል ተብሎ ለዚሁ ስራ 3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተጠይቆ 2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚሆን ገንዘብ ተለቋል፡፡ ለሁሉም የክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች ለ2001 በጀት አመት ዕቅዳቸውን ሳያቀርቡና በሪቪው ቦርድ ሳይታይ ከአለም ባንክ (EMSAP II) ብር 16,700,000.00 (አስራ ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ብር) ተለቆላቸው ተገኝቷል፡፡

25 ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ ፕሮጀክቱ ሲጀመር የሦስት ዓመቱ በጀት በሁለት ዓመት/ ከዚያ ባነሰ ለማጠናቀቅ ይቻላል በሚል አምነት ስምምነት ተደርሶ እያንዳንዱ ክልል እና ፈጻሚ አካላት ፕላን አቅርቦ በዓለም ባንክ ጸድቆ ለክልሎች እንዲሰራጭ ተደርጓል ቢሉም እኛ ከቀረበልን መረጃ ለመረዳት እንደቻልነው የቀረበው እቅድ የአንድ አመት (የ2000 ዓ.ም.) ብቻ መሆኑን ነው፡፡

<u>ፈንድ በተገባው ስምምነት መሰረት የማይለቀቅ ስለመሆኑ</u>

26 በናሙና በተመረጡ አስፈፃሚ አካላት ፈንድ በውሉ መሰረት በተቀመጠው ጊዜ የማይለቀቅ እና ዘግይቶ ከተለቀቀ በኋላም በአጭር ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን እንዲያወራርዱ ጫና

የሚደረግ መሆኑን ከተገኙ መረጃዎች እና አስፈጻሚ መ/ቤቶች ከሰጡት መግለጫዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

27 ከፑል ፈንድ (Pool fund) ብር 1,293,430.00 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ሦስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ብር) በህዳር 2001 ተሰብስቦ ነገር ግን እስከ ግንቦት 2001 ዓ.ም. ለአስፈጻሚ አካላት አልተሰራጨም፡፡ የግሎባል ፈንድ ሰባተኛ ዙር አንደኛ ዓመት ቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል አገልግሎት፣ ከፌዴራል የኤች.አይ.ቪ/.ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት በጥር ወር መጨረሻ እና በየካቲት ወር መጀመሪያ 2001 ዓ.ም. ለክልል የኤች.አይ.ቪ/.ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት የተላለፈ ብር 18,892,689.00 (አስራ ስምንት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና ሁለት ስድስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ) እስከ ህዳር 27 ቀን 2003 ዓ.ም. ለወረዳ ጤና ጽ/ቤት እና ለጤና ተቋማት መተላለፍ ሲገባው አልተላለፈም፡፡

28 የሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የጤና ተቋማት ግንባታን እና ለጤና መረጃ አያያዝ ሥርዓት ዝርጋታ ተግባር የሚውለው በጀት የሥራውን ዝርዝር ሁኔታና ኃላፊነት የሚወስደው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነው፡፡ ከግሎባል ፈንድ ከተገኘ ገንዘብ ለዚህ ተግባር የሚውለው በጀት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደተላለፈ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያው መሰረት ለማንኛውም አስፈጻሚ አካል ፈንድ ሲለቀቅ በመጀመሪያ በተጠየቀው ገንዘብ ምን እንደሚያሰራ የሚያሳይ ዝርዝር ዕቅድ ማቅረብ ስለሚኖርበት የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

29. እንዲሁም የጋምቤላ የኤች.አይ.ቪ/.ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት የግሎባል ፈንድ 7ኛ ዙር ፈንድን ለመጠቀም ውል ከተፈራረሙ በኋላ ውሉ ጠፍቷል ተብሎ ድጋሚ ሌላ ውል የተፈራረሙ ሲሆን በመጀመሪያው ውል መሰረት ያቀዱትን ሥራ በወቅቱ መሥራት አለመቻሉን ጽ/ቤቱ ገልጿል፡፡

30. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው፣ ለጋሾች ገንዘብ ከመልቀቃቸው በፊት መሟላት ያለባቸውን ጉዳይ ስለሚያጣሩና በተለይም ያልተወራረደ ሂሳብ መጠን፣ ሂሳቡ ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ሪፖርት እንዲቀርብላቸው ስለሚፈልጉ፣ ከለጋሾች ገንዘብ በተጠየቀበት ወቅት የማይለቀቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በተጠየቁበት ወቅት ተሟልተው ካልተገኙ ወይንም ሂሳቡ እንዲወራረድ በተጠየቀበት ጊዜ ካልተወራረደ ፈንዱን ከመልቀቅ እንደሚዘገይና፣ በተጨማሪም በአራተኛው ዙር አራተኛ ዓመት ግሎባል ፈንድ ገንዘብ ለመልቀቅ፣ የቋሚ ንብረት መዝገብ (Fixed

Assest Registration) እና የኦዲት አስተዳደር ምላሽ (Audit Management Response) መለኪያ በመደረጉና ክልሎች በተጠየቀው ጊዜ በወቅቱና በጥራት ባለመላካቸው ጊዜ በመውሰዱ የተከሰተ ችግር እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

31. የሰባተኛው ዙር የመጀመሪያው ምዕራፍ አንደኛው ዓመት ውል በአንድ በኩል (በጋምቤላ ክልል) ተፈርሞ በሁለተኛው ወገን ሳይፈረም የት እንደደረሰ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ግን ገንዘቡ ያልተለቀቀበት ምክንያት፤ የውል ስምምነት ያለመፈረሙ ሳይሆን በወቅቱ ወደ ክልሉ ሙያዊ እገዛ ለመስጠት ከማዕከል (ከጽ/ቤቱ) የተንቀሳቀሰው ቡድን ባደረገው ዳሰሳ፤ የአራተኛው ዙር ሶስተኛ ዓመት ግሎባል ፈንድ (Global Fund) የተለቀቀው ገንዘብ ሳይንቀሳቀስ  በባንክ ተቀምጦ በማግኘቱ እና ሪፖርት በማድረጉ፤ የሰባተኛው ዙር የመጀመሪያው ምዕራፍ አንደኛው ዓመት ገንዘብ ለጊዜው እንዲዘገይ በመደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

32. ጽ/ቤቱ በመቀጠል እንደገለጸው እንደ ግሎባል ፈንድ (Global Fund, GF) ውል/ሕግ መሰረት ገንዘብ ለፈጻሚ አካላት የሚለቀቀው ሁሉም ክልሎች  ማግኘት መብታቸው ሆኖ ሳይሆን አፈጻጸማቸውን መሰረት አድርጎ (Performance Base) መሆን ነበረበት፡፡ ሆኖም የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት በተለይም ለክልሎች የመንግሰት ፈጻሚ አካላት በመሆናችው የተገኘው ገንዘብ ለሁሉም ክልሎች እየተሰራጨ ይገኛል፡፡ ይኸ እንደዚህ እንዳለ  የግራንት ውል ስምምነቱ ተፈርሞ ቀደም ሲል ለሌሎች ክልሎች ተለቆ ለጋምቤላ ያልተለቀቀው በፊት ከወሰደው ገንዘብ 75% የሚሆነውን ስላወራረደ መሆኑን ነገር ግን ለሌሎች ክልል ጤና ቢሮዎች ከሰባተኛ ዙር ከቀራቸው ገንዘብ  13% ሲለቀቅ ለጋምቤላም ተጠቃሎ እንዲለቀቅ ተደርጓል ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከወሰዱት ፈንድ ውስጥ 75% የሚሆነውን ሳያወራርዱ ለሌሎች አስፈጻሚ አካላት ፈንድ እንደሚለቀቅቀ በኦዲቱ ወቅት በመታውቁ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

33. የችግሩ መንስዔ መስፈርቱ ላይ የተቀመጡትን ግልጽ መመሪያዎች ባለመከበራቸው ሲሆን፣ ይኸውም አስፈፃሚ አካላት እናከናውነዋለን ብለው ያቀረቡት የሥራ ወይም የፕሮጀክት ሃሳብ የዕቅድ ገምጋሚ ባለሙያዎች የዕቅዱን ተቀባይነት እና ተፈጻሚነቱን አስተያየት ሳይሰጡበት በጽ/ቤቱ ገንዘቡ በመለቀቁ ነው፡፡ ስለሆነም አሠራሩ ወደ ተግባር ሊለወጡ ለማይችሉ የፕሮጀክት ሃሳቦች ጭምር ፈንድ ለመልቀቅ በር እንዲከፍት አድርጓል፡፡

34. በአጠቃላይ ለአስፈፃሚ አካላት ገንዘብ ሲለቀቅ መሟላት ያለባቸዉን መረጃ (የሥራው ዓይነት እና ዋጋ ፣ሥራዉ የት እንደሚከናወን፣ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅ እና ተጨማሪ ገንዘብ ሲጠየቅ ሥራው የሚገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታውን የሚያሳይ መረጃና በመጀመሪያው በታቀደው ገንዘብ መጠን ለምን እንዳልተጠናቀቀ ምክንያቱ) እንዲቀርብ እና፣ በስምምነቱ መሠረት በወቅቱ እንዲለቀቅ ባለመደረጋቸው፣ ገንዘቡ ከተላለፈ በኋላም በቂ ክትትል ባለመደረጉና እንዲሁም የማስፈጸሚያ መመሪያዎች ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ባለመደረጉ ሥራዎች በታቀደው መሠረት እንዳይከናወኑ ወይንም ክንውን ከዕቅድ በታች እንዲሆኑ ማድረጉና ፈንዱን በወቅቱ ሥራ ላይ አውሎ ሂሳቡንም በፍጥነት እንዳይወራረድ አንዱ ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>አስፈጻሚ አካላት የተለቀቀላቸውን ፈንድ ከሀገር አቀፉ የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ (CCM) ፈቃድ ውጭ የሥራ ለውጥ (ሪፕሮግራም) የሚያደርጉ ስለመሆኑ፣</u>

35. ጽ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ስም ለአስፈጻሚ አካላት የሚለቀቀውን ገንዘብ ለተፈቀደት ተግባር ብቻ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ አለበት ፡፡ አስፈጻሚ አካላት የተለቀቀው ፈንድ ከተፈቀደው ተግባር ውጭ ለማዋል የሥራ ለውጥ ለማድረግ (ሪፕሮግራም) ሲፈልጉ፣ መጀመሪያ ለጠዩቁት ተግባር ለምን ሊያውሉት እንዳልቻሉ እና ወደ ሌላ ሥራ መቀየር እንዳስፈለጋቸው አሳማኝ ማስረጃ ለሀገር አቀፉ የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ (Country Coordinaation Mechanism,CCM) (አባላቱ በአባሪ 2 ላይ ተያይዟል) በማቅረብ ፈቃድ ሳያገኙ ፈንዱን ከተፈቀደለት ተግባር ውጭ ማዋል የለባቸውም፡፡

36. እንደዚሁም የግሎባል ፈንድ የኢትዮጵያ ወኪል የሆነው UNOPS ከተሰኘው ድርጅት በተገለጸልን መሠረት ግሎባል ፈንድ የፕሮግራም ለውጥን (ሪፕሮግራሚንግን) እንደማይደግፍ የግድ አስገዳጅ ከሆነም ለአገር አቀፉ የፈንድ ማስተባበሪያ ዘዴ ቀርቦ መጽደቅ እንደሚኖርበት ገልጿል። ይሁን እንጂ የሀገር አቀፉን የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ ፈቃድ ሳያገኝ በአጠቃላይ ብር 201,449,630.00 (ሁለት መቶ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አርባ አራ ሺህ ስድስት መቶ ሠላሳ ብር) እና የአሜሪካ ዶላር 1,623,466 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሦስት ሺህ አራት መቶ ስድሳ ስድስት የአሜሪካን ዶላር) በተለያዩ መ/ቤቶች

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

እና በክልል ጽ/ቤቶች ከተፈቀደለት ተግባር ውጭ ወደ ሌላ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | ያዛወረው መ/ቤት | የተፈቀደለት ተግባር | የተዘዋወረበት | የገንዘቡ መጠን በብር |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የኢትዮጵያ ጤና እና ስነ-ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት | ሕዝብ ላይ ያተኮረ የኤች.አይ.ቪ. ጥናት (Population Base HIV Survey) | ለጤና ተቋማት ግንባታ | 2,607,390.00 |
| | | ለላብራቶሪ መሣሪያዎች (Laboratory Equipments) መግዣ | ለጤና ተቋማት ግንባታ | 15,038,674.00 |
| 2 | የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | ለፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድኃኒት (ARV Drugs) መግዣ | ለጤና ተቋማት ግንባታ | 71,675,311.00 |
| | | ለቴሌ ሜዲስን | ለጤና ተቋማት ግንባታ | 50,141,406.00 |
| | | ለተጓዳኝ በሽታ እና ለአባለዘር በሽታ | ለፀረ-ኤችአይ.ቪ. መድኃኒትና ለልዩ ፋርማሲ | 37,663,447.00 |
| | | ለቢሮ ዕቃዎች ግዥ | ለልዩ ፋርማሲና ለሥርጭት ወጪ (Distrubition Cost) | 4,842,322.00 |
| | | ለመኪና፣ ለሞተር ሳይክልና ለባይስክል | ለጤና ተቋማት ግንባታ | 6,527,469.00 |
| | | ለተለያዩ አስተዳደራዊ ወጪዎች | ለሥርጭት (Distrubition Cost) | 37,328.00 |
| 3 | የትግራይ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤት | ቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎት | ለጤና ተቋማት ግንባታ | 12,916,283.00 |
| | | | ድምር | 201,449,630.00 |
| 4 | የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ | ለተሽከርካሪዎች ግዥ | ለመድኃኒት ማከማቻ እና ቢሮዎች ግንባታ | 1,623,466.00 (የአሜሪካ ዶላር) |

37. አስፈጻሚ አካላት ለምን ሳያስፈቅዱ ሪፐሮግራም እንደሚያደርጉ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤት ፈንድ በወቅቱ ስለማይለቀቅላቸው ያቀዱትን ተግባር በጊዜው ለማከናወን ከሌሎች ለጋሽ አካላት በሚገኝ ገንዘብ የሚጠቀሙ እና ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት ዘግይቶ የሚመጣውን ገንዘብ ደግሞ ለሌላ ፕሮግራም ለማዋል ሪፕሮግራም እንዲያደርጉ ሲጠይቁ፣ ያለው ሂደት አሰልቺ እና ፈንድ ከተለቀቀ በኋላም ለተባለለት አላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ያለው ክትትል ደካማ በመሆኑ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ለአገር አቀፉ የፈንድ ማስተባበርያ ዘዴ (CCM) አቅርበው ፍቃድ ሳያገኙ ከታቀደው ተግባር ውጭ ለሌላ ተግባር የሚያውሉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

38. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ በጤና ጥበቃና በሥሩ ባሉ መ/ቤቶች አማካኝነት የሥራ ለውጥ የተደረገባቸው ሁሉም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በወሰነው መሰረት ቁጥጥር ባለው ሁኔታ የጤና ሥርዓቱን ለመገንባት ሲባል ከተለያዩ ርዕሶች ገንዘቡ ወደ ግንባታ እንዲዞር መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ፈንዱ መጀመሪያ ለተጠየቀበት ተግባር ለምን እንዳልዋለ እና የፕሮግራም ለውጥ ሲደረግ ለአገር አቀፉ የፈንድ ማስተባበርያ ዘዴ ቀርቦ እንዲፈቀድ እንዳልተደረገ ግን የሰጡት ምላሽ የለም፡፡

39. ስለሆነም አሠራሩ ፕሮፖዛል እና የሥራ ዕቅድ ቀርቦ ፈንድ ከተለቀቀ በኋላ አሳማኝ ምክንያት ሳይቀርብ እና ፈንዱን የአገር አቀፉ የፈንድ ማስተባበሪያ ዘዴ ሳይፈቅድ ለሌላ ተግባር እንዲውል መደረጉ መጀመሪያም ፈንዱ ሲለቀቅ በበቂ ጥናት የተፈቀደ አለመሆኑን ከማመልከቱም በላይ ሁኔታው ከቀጠለ አገሪቱን ተጨማሪ ፈንድ እንዳታገኝ ሊያደርግ ስለሚችል አልተቀበልነውም፡፡

**<u>ጽ/ቤቱ ፈንድ ለአስፈጻሚ አካላት ሲሰጥ የተሰጣቸውን ፈንድ የሚያወራርዱበት ጊዜ ተወስኖ በውሉ ላይ የማይቀመጥ ስለመሆኑ እና ቀድሞ የተሰጠ ሳይወራረድ ተጨማሪ ፈንድ ስለመለቀቁ፤</u>**

40. ከኤች.አይቪ./ኤድስ ጋር በተያያዘ የሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት ለዚሁ ተግባር የሚውል ፈንድ ጽ/ቤቱን ሲጠይቁ በፈንዱ ሊያከናውኑ ያቀዱት ዝርዝር ተግባራትን የሚያሳይ የድርጊት መርሃ ግብር ማቅረብ አለባቸው፡፡ የድርጊት መርሃ ግብሩም ለእያንዳንዱ ሥራ ምን ያህል ዝርዝር ወጪ እንደሚያስፈልግ በግልጽ ማሳየት ይኖርበታል፡፡ አስፈጻሚ አካላት የተሰጣቸውን የፈንድ ሂሳብ የሚያወራርዱበት ጊዜ እንደ የሥራው ሁኔታ የሚወራረድበት ጊዜ ተወስኖ በውሉ ላይ ሊቀመጥ ይገባል፣ ሂሳቡም በውል ስምምነቱ መሰረት መወራረድ አለበት፡፡ ቀጣይ ፈንድ መለቀቅ የሚኖርበት ደግሞ መጀመሪያ የተለቀቀው ሂሳብ ሲወራረድ ብቻ መሆን አለበት፡፡

41. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለክልሎችም ሆነ ለሌሎች አስፈጻሚ አካላት ፈንድ ሲጠይቁ የሚሰሩትን ሥራ በዝርዝር የሚያቀርቡ ቢሆንም፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ግን ምን ያህል ወጪ እንደሚፈልጉ ዝርዝር እንደማያቀርቡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ውሎች ለመረዳት ተችሏል፡፡


42. ከግሎባል ፈንድ 2ኛ ዙር የአሜሪካን ዶላር 10,000,000.00 (አሥር ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) 4ኛ ዙር የአሜሪካን ዶላር 24,837,308.00 (ሃያ አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ስምንት የአሜሪካን ዶላር) በድምሩ የአሜሪካን ዶላር 34,837,308.00 (ሠላሳ አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ስምንት አሜሪካን ዶላር) ሂሳብ በወቅቱ ባለማወራረዱ የተነሳ ገንዘቡ ሳይለቀቅ የጊዜ ገደቡ ማለፉ ታውቋል፡፡

<u>ከግሎባል ፈንድ በተለያየ ዙር ተሰጥቶ ሳይወራረድ የቆየ ገንዘብ የሚያሳይ ሠንጠረዥ</u>

| ተ.ቁ | ዙር | ያልተወራረደ የገንዘብ መጠን በብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1. | 2ኛ ዙር | 4,456,867.00 | የዕርዳታ ውል ስምምነት ጊዜው የተጠናቀቀ |
| 2. | 4ኛ ዙር | 395,209,405.00 | የዕርዳታ ውል ስምምነት ጊዜው የተጠናቀቀ |
| 3. | 7ኛ ዙር | 352,754,077.00 | |
| | ድምር | 752,420,349.00 | |

43. ከዚህ ውስጥ በዙር ሁለት ብር 51,514 (ሃምሳ አንድ ሺህ አምስት መቶ አስራ አራት ብር)፣ በዙር አራት 337,597,237 (ሦስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሰባት ብር) እና በዙር ሰባት 286,675,391 (ሁለት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና አንድ ብር) በድምሩ ብር 624,324,142 (ስድስት መቶ ሃያ አራት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃያ አራት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሁለት ብር) ማለትም ካልተወራረደው ገንዘብ 83% የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይይዛል፡፡ (ሥርጭቱን በተመለከተ ከታች ያለውን ግራፍ ይመልከቱ)

<u>በዙር ሁለት፣ በዙር አራት እና በዙር ሰባት በክልሎች መንግሥታዊ በሆኑ እና መንግሥታዊ ባልሆኑመ/ቤቶች እና በጤና ጥበቃ እና በሥሩ ያሉ መ/ቤቶች ያልተወራረደ ገንዘብ</u>




44. ለተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት መግዣ (የአባላዘር በሽታዎችን ጨምሮ) የአሜሪካን ዶላር 18,075,856.00 (አስራ ስምንት ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ስድስት አሜሪካን ዶላር) ወይም ብር 175,492,922.00 (አንድ መቶ ሰባ አምስት ሚሊዮን አራ መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ብር) ተመድቧል፡፡ ነገር ግን የስምምነቱ ጊዜ ካለፈ በኋላ ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ የአሜሪካን ዶላር 17,088,715 (አስራ ሰባት ሚሊዮን ሰማኒያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ አስራ አምስት የአሜሪካን ዶላር) ወይም ብር 166,922,559.00 (አንድ መቶ ስድሳ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ብር) ማለትም 94% የሚሆነው ሂሳብ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2003 ዓ.ም. (ሴፕቴምበር 9 2010) ድረስ አልተወራረደም፡፡

45. በውጭ እና በውስጥ ኦዲተሮች በተገኘ ግኝት በአፋር የEMSAPII ፈንድ ቢ ዘርፈ ብዙ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምላሽ /Melti-Sectoral HIV/AIDS Responce/ በፊት የወሰዱትን ብር 44,764.00 (አርባ አራት ሺህ ሰባት መቶ ስድሳ አራት ብር) ሳያወራርዱ ሌላ ተጨማሪ ብር 37,500.00 (ሰላሳ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር) መለቀቁ እና በሶማሌ

420,615.00 (አራት መቶ ሃያ ሺህ ስድስት መቶ አርባ አምስት ብር) እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት 3,668,953.00 (ሦስት ሚሊዮን ስድስት መቶ ስድሳ ስምንት ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሦስት ብር) ለአስፈፃሚ አካላት የተለቀቀዉ ሂሳብ በድምሩ ብር 4,089,568.00 (አራት ሚሊዮን ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ስድሳ ስምንት ብር) ሳይወራረድ ሌላ ተጨማሪ ፈንድ መለቀቁ ተረጋግጧል፡፡

46. የፌዴራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው የውል ስምምነቱ በዝርዝር የገንዘቡን መጠን፣ የሚከናወኑ ተግባራት፣ የሚያወራርዱበት ጊዜ ወዘተ..እንደሚይዝ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ይህንን በኦዲቱ ወቅት ከቀረቡልን ውሎች ውስጥ ስላልተገኘ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡ ወጥ የሆነ የጊዜ ገደብ የውል ስምምነቱ ላይ የማይቀመጥበትን ምክንያትም ዋናው ትኩረት ገንዘቡን በፍጥነት ሥራ ላይ አውሎ ማወራረድ በመሆኑና ገንዘብ ለተለቀቀላቸው አካላት በሙሉ ብሎም ለክልል መስተዳድር ኃላፊዎች በየወቅቱ ገንዘቡን ለታለመለት ዓላማ ሥራ ላይ በማዋል ሂሳቡ እንዲወራረድ በመግለጽ በደብዳቤ የሚያሳውቁ ስለሆነ የጊዜ ገደብ ማስቀመጡ ጠቃሚ ባለመሆኑና መንግስታዊ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት የወሰዱትን ገንዘብ ባያወራርዱም ገንዘቡ እንደሚሰጣቸው አስታውቀዋል፡፡ በመቀጠልም ገንዘቡ አካውንታቸው ውስጥ መቀመጡ በራሱ ራሱን የቻለ አሉታዊ ችግሮች አሉት ብለዋል፡፡ ሥራ ላይ ሳይውል ወደ ግሎባል ፈንድ ስለተመለሰው ገንዘብ በሰጡት መልስ ገንዘቡ የተመደበው ለፀረ-ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መድኃኒት (ARV) መግዣ ሲሆን የታቀደው ዕቅድ ከፍ ያለ ሴለነበር ገንዘቡ የተመለሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

47. ይሁን እንጂ ማንኛውም ፕሮጀክት የሚጀመርበት ቀን እና የሚያልቀበት ቀን በግልጽ መቀመጥ እና ይህም በውሉ ላይ መታየት የሚገባው በመሆኑ፣ እንዲሁም ገንዘቡ አካውንታቸው ውስጥ እንዳይታይ ሲባል ብቻ በፊት የተወሰደ ገንዘብ ሥራ ላይ ሳይውል እና ሳይወራረድ ተጨማሪ መስጠት ተገቢ ባለመሆኑ የተሰጡትን መልሶች አልተቀበልናቸውም፡፡ በመሰረቱ ዕርዳታው ሥራ ላይ እንዲውሉ መጣር እና ማበረታታት ሥራ ላይ ሳይውሉ የሚመለሱ ገንዘቦች እንኳ ቢኖሩ ሌላ የሥራ ዕቅድ በማቅረብ በገንዘቡ አገሪቱ ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ በተገባ ነበር፡፡ የተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት ግዥን በተመለከተ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ገንዘቡ ሳይወራረድ መዘገየቱን ገልጸዋል፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊዎች በተላለፈላቸው

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ገንዘብ መድኃኒቱ ለምን እንዳልተገዛ እና ወደ ጤና ተቋማት እንዳልተሠራጨ ተጠይቀው ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አልሰጡም፡፡

48. እንደዚሁም የጊዜ ገደቡ በውሉ ላይ ባለመቀመጡ አስፈጻሚ አካላት የወሰዱትን ፈንድ በፈቀዱት ጊዜ ገንዘቡን ሥራ ላይ እንዲያውሉት፣ ሥራ ላይ አውለውትም ቢሆን እንኳ፣ ሂሳቡን እንዳያወራርዱ ወይም ሥራ ላይ ሳያውሉት ገንዘቡን እንዲያስቀምጡት ወይም ለሌላ ሥራ እንዲያውሉት የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ጽ/ቤቱም ለክትትልም ሆነ ቀጣይ ፈንድ ለመልቀቅ እና በወቅቱ የወሰዱትን ፈንድ እንዲያወራርዱ ለማድረግ አዳጋች አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም ለጋሽ አካላት ቀጣይ ፈንድ የሚለቁት ሥራ ላይ ውሎ በተወራረደው የገንዘብ መጠን ስለሆነ የሚፈለገው ተመጣጣኝ ገንዘብ በወቅቱ እንዳይተካ፣ ከማድረጉም በላይ በለጋሽ አካላት ገንዘቡ አይሰራበትም የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ እና ቀጣይ በሚለቀቀው ፈንድ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

<u>በኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት ስለሚፈልጉ ወገኖች ብዛት መጠን የተደረገ ጥናት ስለአለመኖሩ፣</u>

49. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት የሚፈልጉት ወገኖች ቁጥር ሊታወቅ ወይም በመገመት በአገልግሎት ሰጪዎች በኩል ሊያዝ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት ተሰጥቶት የቫይረሱን ስርጭት የሚዳስስ ጥናትና የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ በሀገሪቱ በፌዴራል ደረጃ እና በናሙና ተመርጠው ጉብኝት በተደረገባቸው ክልሎች በኤች.አይቪ. ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት የሚፈልጉ ወገኖች ዙሪያ የተጠና ጥናት የለም፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ሕዝብን መሰረት ያደረገ የኤች.አይ.ቪ. ጥናት (Population Base HIV Survey) ለማካሄድ የአሜሪካን ዶላር 546,395 (አምስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና አምስት የአሜሪካን ዶላር) ተመድቧል፡፡ ነገር ግን ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ የአሜሪካን ዶላር 300,000 (ሦስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) የሚሆነው ውሉ ተሰርዞ ወደ ሌላ ተግባር እንዲዞር ተደርጓል፣ በቀሪውም አሜሪካን ዶላር 246,395.00 (ሁለት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና አምስት የአሜሪካን ዶላር) የተጠና ጥናት ወይም የተሰራ ሥራ ለመኖሩ የቀረበ መረጃ የለም፡፡

51. በኦዲቱ ወቅት ለኤድስ ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የቫይረሱ ስርጭት የሚዳስስ ጥናት ከአማራ ክልል በስተቀር በሌሎቹ ክልሎችም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የተጠና ጥናት የለም፡ እንዲሁም ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችም የሚያገለግል የአፈፃፀም መመሪያ አልተዘጋጀም፡፡ እንደዚሁም ለአደጋ ተጋላጭና ወላጅ ላጡ ህፃናት (OVC situation analysis) ላይ የተባበሩት መንግስታት የሕጻናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) ጥናት እንዲጠና ብር 1,000,000.00 ( አንድ ሚሊዮን ብር) ለቀድሞው የሴቶች ጉዳይ ሚንስቴር የተሰጠ ቢሆንም ሥራ ላይ አለመዋሉ ታውቋል፡፡

52. ስለሆነም በጽ/ቤቱና በአስፈጻሚ አካላት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት የሚፈልጉትን ወገኖች ቁጥርና የቫይረሱ ስርጭት ጥናት ባለመከናወኑ አገልግሎቱን ለመጠቀም የሚፈልጉ ሰዎች ብዛት መጠንና፣ የአገልግሎቱ ሽፋን መጠን ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ አያስችልም፡፡ እንዲሁም ለበሽታው ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተመለከተ ሊዘጋጅ የሚገባው የአፈፃፀም መመሪያ ባለመዘጋጀቱ እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች ለመርዳት የሚደረገውን ጥረት በሥርዓትና በተገቢው መንገድ መሆኑን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

53. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ጥናቱ በተለያዩ ምክንያቶች የተጓተተ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ጥናቱን ለማካሄድ ፕሮቶኮል የተዘጋጀ፣ አስተበባሪ ኮሚቴ እና አጥኚ ቡድን ተቋቁሞ ሥራው መጀመሩን ገልጸዋል፡፡ የቀድሞው የሴቶች ጉዳይ ሚንስቴር ኃላፊዎች ደግሞ ሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ በሚቀጥለው በጀት ዓመት ለመጠቀም ዕቅድ እንደያዙ ገልጸዋል፡፡

54. ይሁን እንጂ እስካሁን ባለው አሰራር በኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት የሚፈልጉትን በቫይረሱ ተጠቂ የሆኑ ወገኖች ቁጥር እና ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የቫይረሱን ስርጭት የሚዳስስ ጥናት አለመኖሩ፣ ፍትሀዊ የግብአት ክፍፍል ለማድረግም ሆነ የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከል፣ ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት የወጣውን የፖሊሲ አቅጣጫ አፈጻጸም ለመለካትና ለመገምገም አያስችልም፡፡

## <u>የተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት (OIT) አቅርቦት የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ቫይረስ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ለሁሉም ስለመዳረሱ፣</u>

55. የተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት (Opportunistic Infectious Treatment, OIT) አቅርቦት የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ቫይረስ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ለሁሉም መዳረስ አለበት። ይህንንም ለማዳረስ በተመደበው ገንዘብ መድኃኒቱ ተገዝቶ ለየጤና ተቋማቱ ሊሰራጭ ይገባል።

56. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በቅድሚያ በአገሪቱ የተጓዳኝ በሽታ መድኃኒት እጥረት መኖሩና የእጥረቱ መጠን ታውቆ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ለሁሉም እንዲዳረስ ለማድረግ ጽ/ቤቱ በዕቅድ ይዞት የነበረ ቢሆንም ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የተዘረጋ ሥርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡ በናሙና ጉብኝት በተደረገባቸው በጋምቤላ፣ በትግራይ፣ እና በአማራ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የሚገኙ ጤና ተቋማት የመድኃኒቱ እጥረት እንዳለባቸው ታውቋል፡፡

57. በአንፃሩ ከግሎባል ፈንድ አራተኛ ዙር (እ.ኤ.አ. 1 ማርች 2005 እስከ 28 ፌብሪዋሪ 2010) ባለው ጊዜ ውስጥ ለተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት መግዣ (የአባላዘር በሽታዎችን ጨምሮ) የአሜሪካን ዶላር 18,075,856.00 (ብር 175,492,922.00) ተመድቧል፡፡ ነገር ግን የስምምነቱ ጊዜ ካለፈ በኋላ ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ የአሜሪካን ዶላር 17,088,715 (አስራ ሰባት ሚሊዮን ሰማኒያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ አስራ አምስት የአሜሪካን ዶላር) ወይንም ብር 166,922,559.00 (አንድ መቶ ስድሳ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት አምስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር) ማለትም 94% በሚሆነው ገንዘብ እስከ ህዳር 30 ቀን 2003 ዓ.ም. መድኃኒቱ ለመገዛቱ ማስረጃ ያልቀረበና ሂሳቡም ያልተወራረደ መሆኑ ታውቋል፡፡

58. ስለጉዳዩ የፌዴራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው የተጓዳኝ በሽታ መድኃኒቶች ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ብቻ ሳይሆን መድኃኒቱ ለሁሉም ታካሚ የሚሰጥ በመሆኑና ችግሩም ካለው ከፍተኛ የሆነ የመድኃኒቱ ፍላጎት የተነሳ በአጭር ጊዜ የሚፈታ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በተመደበው ገንዘብ መድኃኒቱ ለምን ተገዝቶ እንዳልተሰራጨ ምክንያት አላቀረቡም፡፡ መድኃኒቱ ለምን እንዳልተገዛም የጤና ጥበቃ ሚንስቴር የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አልሰጡም።


59. የተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖችም ሆነ ለሌሎች ህሙማን አስፈላጊ መሆኑና ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለ እየታወቀ ለዚሁ ተብሎ በተመደበው ገንዘብ መድኃኒቱ ተገዝቶ አለመሰራጨቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ቫይረሱ በደማቸዉ ዉስጥ ያለ ነፍሰጡር እናቶች</u>
<u>ቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ</u>
<u>የመከላከል አገልግሎትን ስለማግኘታቸው፣</u>


60. ከ2000 እስከ 2003 በታቀደው በባለብዙ ዘርፍ የድርጊት ምላሽ መርሃ ግብር መሰረት ኤች.አይ. ቪ. በደማቸዉ ዉስጥ ያለ ነፍሰጡር እናቶች ቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎት 80% የሚሆኑት እ.ኤ.አ. በ2010 መጨረሻ ማግኘት አለባቸው፡፡ አገልግሎቱም በአገሪቱ ውስጥ በሁሉም አካባቢ መዳረስ አለበት፡፡

61. ይሁን እንጂ ቫይረሱ በደማቸው ከሚገኝ እናቶችና አገልግሎቱን ማግኘት ከሚገባቸው በ2002 ዓ.ም. አገልግሎቱን ለመስጠት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም 8.3% እናቶች ብቻ አገልግሎቱን ያገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

62. በናሙና በተመረጡና ጉብኝት በተደረገባቸው ክልሎች፤ በአማራ ክልል ከሚገኙ 1497 የጤና ተቋማት ውስጥ በ276 (18%)፣ በትግራይ ክልል 223 የመንግስት የጤና ተቋማት መካከል በ104 (47%)፣ በጋምቤላ ክልል 51 ጤና ተቋማት ውስጥ በ9 (18%)፣ በኦሮሚያ ክልል 1049 ጤና ተቋማት ውስጥ በ 306 (29%)፣ በአዲስ አበበ ከተማ መስተዳደር ከሚገኙ 573 የጤና ተቋማት መካከል በ58 (10%) ብቻ አገልግሎቱ እንደሚሰጥ ተገልጿል፡፡



63. በአገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ ደግሞ፣ በአገሪቱ ውስጥ ባሉ የግልና የመንግስት ጤና ተቋማት አገልግሎቱ የሚሰጠው በ1352 ተቋማት ብቻ ነው፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ምን ያህል የመንግስት እና የግል የጤና ተቋማት እንዳሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተጠይቆ፤ ይህ የኦዲት ሪፖርት እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ ስላልተሰጠ ተጨማሪ ትንተና መስራት አልተቻለም፡፡




64. በሌላ በኩል በመርሃ ግብሩ መሰረት ቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎት በዕቅድ ዘመኑ ከተያዘው 80% ሽፋን ውስጥ የግል ጤና ተቋማት ድርሻ አነስተኛ ነው፡፡ ሽፋኑ አነስተኛ የሆነበትን ምክንያት ለማወቅ የተደረገ ጥናት፣ ክትትልና ግምገማ ለኦዲቱ ሥራ ባለመቅረቡ ተጨማሪ አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

65. በአንፃሩ ደግሞ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ዉስጥ ያለ ነፍሰጡር እናቶች ቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ ለመከላከል አገልግሎት ሥራ ተብሎ ለትግራይ ክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት የተመደበው ገንዘብ ወደ ጤና ተቋማት ግንባታ የዞረ መሆኑ ታውቋል፡፡

66. ስለጉዳዩ የጽቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ "በመጀመሪያ ዕቅዱ ከፍ ብሎ የተቀመጠው አገሪቷ ሁሉን አቀፍ ተደራሽነትን ለማሳየትና ለዚህም በቂ ሀብት ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ለማግኘት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ተቋማት አገልግሎቱን እንዲሰጡ ለማድረግ በቅድሚያ መሠራት የሚገባቸው ሥራዎች በመኖራቸው ነው፡፡ ይህንንም ዕውን ለማድረግ በሚቀጥለው ሁለተኛው የአምስት አመት ዕቅድ ውስጥ መያዙን፣፤ አገልግሎቱም

የሚፋጠንበትንም ሁኔታ ከጤና ጥበቃ ሚንስቴር ጋር በመነጋገር አገልግሎቱ የሚፋጠንበት ሥራ በመሠራት ላይ ነው” ብለዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ መጀመሪያውኑ ዕቅድ ሲታቀድ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል እና ሊገኝ የሚችለውን ሀብት ከግምት ውስጥ ማስገባት ነበረበት፡፡ በተጨማሪም ዕቅዱን መሰረት በማድረግ በተገኘው ሀብት በመጠቀም አሁን ባሉት የጤና ተቋማት እንኳን አገልግሎቱ በሙሉ እየተሰጠ ባለመሆኑ ይልቁኑም ለዚህ ተግባር ተብሎ የተመደበው ሀብት ለሌላ ተግባር በመዋሉ ረገድ የሰጡትን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

67. ይሁን እንጂ፣ ተግባራዊ እንደማይሆን እየታወቀ ከፍተኛ ገንዘብ በዕቅድ መያዙና ከተፈቀደም በኋላ ጽ/ቤቱ አስፈጻሚ አካላትን በማስተባበር እና በመቀናጀት የተመደበውን ሃብት በመጠቀም ባሉት የጤና ተቋማት አገልግሎት ለመስጠት ጥረት ከማድረግ ይልቅ ለሌላ አገልግሎት ማዋሉ አግባብ ካለመሆኑም በላይ፤ በዚህ ምክንያት ቫይረሱ እንዳይተላለፍ ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት የሚቀንስ፣ የአገልግሎት ሽፋን እንዳያድግ ከማድረጉም በላይ ሁኔታው በለጋሽ ድርጅቶች ቢታወቅ ዕርዳታው ሊቋረጥ ሚችልበት ክስተት የሚፈጥር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

**<u>በፌዴራልም ሆነ በክልል የመረጃ አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና ልውውጥ ሥርዓት እንዲሁም የወጪ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርቶች ትክክለኛነት በተመለከተ</u>**

68. በኤች.አይ.ቪ.ኤድስ ዙሪያ የሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት ለወሰዱት ፈንድ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ የስራ አፈጻጸምም ሆነ የወጪ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡ የሚያቀርቡትም ሪፖርት በፈረሙት ውልና እንሰራዋለን ብለው ካቀረቡት የሥራ ዕቅድ መሰረት መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
69. ይሁን እንጂ ተገቢው መረጃ የማይቀርብና ያሉትንም መረጃዎች በወቅቱ ያለመላክ ችግር መኖሩ በናሙና በተመረጡና የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው የአማራ፣የትግራይ፣የኦሮሚያ እና የጋምቤላ ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በሚገኙ ተቋማት ታውቋል፡፡
70. እንደዚሁም ለጤና መረጃ አያያዝ ስርዓት ዝርጋታ (Health Managemnet Information System,HMIS) ብር 26,644,800.00 (ሃያ ስድስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ አራት

ሺ.ህ ስምንት መቶ ብር) የሚሆን ፈንድ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተለቀቀ ቢሆንም፣ በናሙና ጉብኝት በአደረግንባቸው የጤና ቢሮዎች ላይም ሆነ በየጤና ተቋማቱ ሥርዓቱ ተዘርግቶ ሥራ ላይ አልዋለም፡፡

71. በሀገር አቀፍ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ዘርፈ ብዙ ምላሽ የክትትልና የግምገማ ዘዴን ለማጠናከር የአገር አቀፍ ምላሽ የመረጃ ሥርዓት (Country Response Information System, CRIS) የተሰኘ ሶፍት-ዌር ላይ ከሁሉም ክልሎች እና ከተለያዩ የሴክተር መ/ቤቶች ባለሙያዎችን ለማሰልጠን ብር 94,865.00 (ዘጠና አራ ሺ.ህ ስምንት መቶ ስድሳ አምስት ብር) ወጪ ተደርጎ 30 ባለሙያዎች ከታህሳስ 12 እስከ ታህሳስ 18/2002 ድረስ ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም በናሙና በመረጥናቸው የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች፣ በዞኖች እና በወረዳ ባሉ ጽ/ቤቶች ሥርዓቱ ተዘርግቶ ሶፍትዌሩ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

72. ጽ/ቤቱ የሚጠቀምበት ጆርናል ቫውቸር አስቀድሞ የታተመና ተከታታይ ቁጥር የተሰጠው ሳይሆን በየጊዜው በኮምፒዩተር የሚታተም መሆኑ ታውቋል፡፡ እንደዚሁም ጽ/ቤቱ ለጤና ጥበቃ ሚንስቴር፣ በፌዴራል ደረጃ ያሉ አስፈጻሚ አካላት፣ ለክልሎች እና ለሌሎች በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ዙሪያ ለሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት የሚሰጠውን ፈንድ በእያንዳንዱ ተቋም ስም የሚመዘግብበት ተቀጽላ ቋት (Subsidary ledger) አላዘጋጀም፡፡ የጽ/ቤቱ የጥራትና ኮምፕላያንስ ዳይሬክቶሬት ይህን በተመለከተ ኦዲት አድርጎ እንዲሻሻል አስተያየት የሰጠ ቢሆንም ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

73. ስለጉዳዩ የፌዴራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው፤ ከክልል ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር የክትትልና የግምገማ ሥርዓቱ ሪፖርት አቀራረቡን ጨምሮ ለማጠናከርና ለማሻሻል ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣ የውስጥ ቁጥር ሥርዓቱን ለማጠናከር በውስጥ እና በውጭ ኦዲተሮች የተሰጡትን አስተያየቶች ለመተግበር ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሶፍት ዌር ዝርጋታውን በተመለከተ፤ ለጊዜው እንዲዘገይ የተደረገና በሌላ በኩል ደግሞ የማህበረሰብ መረጃ ሥርዓት (Community Information System,CIS) በተሰኘ ሥርዓት መረጃን ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ በመሆኑ በቅድሚያ ሥልጠናው የተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ለጤና አስተዳደር መረጃ ሥርዓት ቀደም ብሎ የተለቀቀውን ፈንድ ለምን ተጠቅመው እንዳልተገበሩ ምላሽ አልሰጡም፡፡ እንደዚሁም የጤና ጥበቃ ሚንስቴርም በተቀበለው ገንዘብ ለምን የጤና አስተዳደር መረጃ

ሥርዓት (HMIS) እንዳልዘረጋ ተጠይቆ ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አልሰጠም፡፡

74. በሌላ በኩል በውስጥ እና በውጭ ኦዲተሮች በተደረጉ ኦዲቶች የተገኙ ግኝቶች ሲታይ፤

- ከአለም ባንክ (EMSAPII) የተገኘውን ፈንድ አስመልክቶ ሁሉም ጆርናል ቫውቸር በኃላፊዎች ያልጸደቁ፣ ከአስፈፃሚ አካላት የተሰበሰቡ አንዳንድ የሂሳብ ማወራረጃ ሪፖርቶች (SOE) በኃላፊ ተፈርመው ያልተላኩ፣ ከክልል የመጡ የወጪ ማጠቃለያ አኃዞች ጠፍተው ሌላ የገንዘብ መጠን የተጻፈባቸው መሆናቸው፣
- ከግሎባል ፈንድ በኦሮሚያ ክልል በዙር አራት በአንደኛ አመት ማጠቃለያ የቀርበው የወጪ ማስረጃ ማጠቃለያ (SOE) ከመረጃ ምንጫቸው ጋር ሲመሳከሩ ብልጫ የሚያሳዩ መሆናቸው፣
- ከአስፈፃሚ አካላት የመጡ አንዳንድ የሂሣብ ማወራረጃ ሪፖርት (SOE) በኃላፊዎች ያልተፈረሙ መሆናቸው፣
- ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤት የወጪ ማጠቃላያው ሪፖርት ካያያዙት የወጪ መረጃ ምንጭ ጋር የተለያዩ መሆናቸው፣ ሁሉም ጆርናል ቫውቸር በኃላፊዎች ያልጸደቁ መሆናቸው፣ በአዲስ አበባ ባሉ ክፍለ ከተሞች ግዢዎች በአስፈላጊ መረጃዎች ማለትም እንደ ግዢ መጠየቂያ፣ የግዢ ማዘዣ፣ የዕቃ ገቢ ማድረጊያ እና ኘሮፎርማ ኢንቮይስ እንደማይያያዙ የተረጋገጡ መሆናቸው፣

በውጭ እና በውስጥ ኦዲተሮች በተጻፉ ሪፖርቶች ላይ ተገልጸዋል፡፡

75. ይሁን እንጂ ከላይ በውስጥ ኦዲትም ሆነ በውጭ ኦዲተሮች በተገኙ ግኝቶች ላይ በጽ/ቤቱ የተወሰደ እርምጃ ለመኖሩ መረጃ አልቀረበም፡፡ በጽ/ቤቱ የሥራ አመራር በቃለ ጉባኤ ቁጥር 11 ላይ የተገለጸ የሂሳብ ማወራረጃ ሪፖርት SOE ለዋና መ/ቤት አቅርበው ለአለም ባንክ የተላከ ነገር ግን የማወራረጃ ሠነዶቹ ያልተገኙና በሂሳብ መዝገብ ያልተመዘገቡ ሂሳቦች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

76. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ከአስፈጻሚ አካላት የሚቀርቡ የፋይናንሻልና የፊዚካል ሪፖርቶች በየመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ

መጸደቃቸው ካልተረጋገጠ በቀር ተቀባይነት ስለሌላቸው በቀጣይነት ሁኔታው እየተጣራ ማስተካከያ እንደሚወሰድ ገልጸዋል፡፡

77. ስለሆነም በጽ/ቤቱ የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱ ወጥ ያለመሆን፣ ጤና ነክ የሆኑትም ሆነ ያልሆኑት መረጃዎች አያያዝ ሥርዓት አለመጠናከር፣ እና ከአስፈጻሚ አካላት ጋር ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመኖር፣ የመረጃ አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና ልውውጡን ደካማ እንዲሆን አድርጐታል፡፡ የሂሳብ መረጃዎችን ምዝገባ ተከታታይ ቁጥርና በታተሙ ጆርናሎች መጠቀም ሲገባና ለእያንዳንዱ አስፈጻሚ አካል የሚሰጠው ፈንድ የሚመዘገብበት ተቀጽላ ቋት (Subsidary ledger) አለመዘጋጀት፣ የወጪ ማስረጃዎች ሆኑ የማጠቃለያ ሪፖርቶች በሚመለከተው ኃላፊዎች አለመጽደቃቸው እንዲሁም የተገዙ ዕቃዎች ገቢ የተደረጉበት ደረሰኝ አለማቅረብ፣ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ ደካማና የውስጥ ቅጥጥር ሥርዓቱ ልል መሆኑን ያመላክታል፡፡

<u>በየደረጃው የሚቀርቡ የአፈጻጸም ሪፖርቶችንና</u>
<u>ሌሎች መረጃዎች ጥራትና በወቅቱ</u>
<u>ስለመቅረባቸው፣</u>

78. በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዙሪያ በተከናወኑ ማንኛዉም ተግባራት ላይ አስፈጻሚ አካላት በየሦስት ወሩ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡ እንዲሁም በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የምክር እና የምርመራ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በመመሪያው ላይ የተቀመጠውን ቅጽ በመጠቀም መረጃውን እየሞሉ በየደረጃው ሊያስተላለፉ ይገባል፡፡

79. ይሁን እንጂ በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዙሪያ በተከናወኑ ማንኛዉም ተግባራት የፋይናንሻልም ሆነ የፊዚካል ሪፖርቶች የጥራት ማነስ፣ ወጥ ያለመሆን፣ ተከታታይ ያለመሆን፣ ድግግሞሽ ያለባቸው እና በየሦስት ወሩ ወቅቱን ጠብቀው እንደማይላኩ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ከፌዴራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ፅ/ቤት የሚላኩ የሪፖርት ፎርማቶቹ ማለትም ቅጾቹ ለመሙላት የማያመቹ መሆናቸውን በአስፈጻሚ አካላት ተገልጿል፡፡ በአስፈጻሚ አካላት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ለሚሠሩ ሥራዎች ጥራቱን የጠበቀ የፋይናንሻልም ሆነ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት እየተጠናቀረ በየሶስት ወሩ አይላክም፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

80. በናሙና ጉብኝት በተደረገባቸው በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የምክር እና የምርመራ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በመመሪያው (VCT guidline) ላይ የተጠቀሰውን የመረጃ መመዝገቢያ ፎርማት እንደማይጠቀሙና ከክልሎች የተላኩት የአፈጻጸም ሪፖርቶች እና በፌዴራል ደረጃ የተጠቃለለው የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችም የተለያዩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

81. በአብዛኛዎቹ አስፈፃሚ አካላት የመረጃ አያያዝ ችግር ያለ ሲሆን፣ በክልል የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት በራስ ተነሳሽነት ሪፖርት ሰርቶ ያለማምጣት ሲጠየቁም ዘግየተው እንደሚልኩ ታውቋል፡፡

82. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች የችግሩ መንስዔ ምን እንደሆነ ተጠይቀው፤ አብዛኛው በክልል ያሉ ወረዳዎች ያሉበት ቦታ ርቀት የተነሳ ሪፖርት በክልል አስተባባሪዎች ለማሰባሰብ ምቹ አለመሆንና እንዲሁም የተለያዩ ፈንዶች ወደ ታች በተወረደ ቁጥር በአንድ አካዉንት ስለሚያዙ፣ የሂሳብ ምዝገባ እና ሪፖርቶች በየሩብ ዓመቱ ስለማይሰሩ መሆን ገልጸዋል። የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ደግሞ ሲመልሱ፤ ችግሩ የተከሰተው ከአገሪቱ ስፋት እና ካለው የመረጃ አሰባበሰብ ስርዓት ጥራት ጉድለት እንዲሁም ከሰው ኃይል ችግር መሆኑን ገልጸዋል። በመቀጠልም በጋራ ግምገማ ወቅት ከክልሎች ጋር በመሆን ሁኔታውን ለማሻሻል እየተነጋገሩበት መሆኑንና ከዚህ ውስጥ ተጠቃሽ የሚሆነው የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ (Monitering and Evaluation Framework) እና የ የማህበረሰብ መረጃ ሥርዓት (CIS) ዝርጋታ ዋናዎቹ መሆናቸውን ገልጸዋል።

83. ይሁን እንጂ መረጃዎች በወቅቱና በጥራት አለመቅረባቸው በአሰራር ላይ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ቶሎ እርምጃ መወሰድ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ አፋጣኝ ምላሽ እንዳይሰጥ ያደርጋል፡፡

## 2.2 በኤች·አይ·ቪ/ ኤድስ ዙሪያ የተገኘውን ፈንድ ለተፈቀዱት ተግባራት ብቻ መዋሉን የሚያረጋግጥ በቂ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

### የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈጻጸም በተመለከተ


84. ጽ/ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሲያዘጋጅ በኤች.አይ.ቪ. ዙሪያ የሚሰሩ አስፈጻሚ አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡ ጽ/ቤቱም ሆነ አስፈፃሚ አካላት የተዘጋጀውን ስትራቴጂክ ዕቅድ ወደ ዓመታዊ ዕቅድ በመመንዘር ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ የስትራቴጂክ ዕቅዱ በትክክል ተግባራዊ ለመሆኑ የክትትል፣ የቁጥጥርና ግምገማ ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

85. ጽ/ቤቱ ከ2000 ዓ.ም. እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ተግባራዊ የሚደረግ አስፈፃሚ አካላት ባሳተፈ መልኩ በባለብዙ ዘርፍ የድርጊት ምላሽ መርሃ ግብር ማዘጋጀቱ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ የስትራቴጂክ ዕቅዱ አፈጻጸም ሲታይ እደሚከተለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

86. የኮንዶም ስርጭትን በተመለከተ በ2000 ዓ.ም 189,500,000.00፣ በ2001 290,000,000.00፣ እንዲሁም በ2002 367,000,000.00 ኮንዶሞች ለማሰራጨት እና በ2010 መጨረሻ በአገሪቱ ያለውን የኮንደም ስርጭትን ወደ 60 ከመቶ ለማሳደግ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ የተሰራጨው የኮንደም ብዛት ግን በ2000 62,500,000.00 (33%)፣ በ2001 97,000,000 (33.4%)፣ በ2002 ደግሞ 127,000,000.00 (34.6%) ነው፡፡ ይህም በሁሉም ዓመታት ከዕቅድ በታች ሲሆን በአጠቃላይ በሦስቱ ዓመታት 846,500,000 ኮንዶም ለማስራጨት ታቅዶ የተሰራጨው 286,500,000 ወይንም 33.8% ሆኖ ተገኝቷል፡፡

87. የሴት ኮንዶም አቅርቦት ከስትራቴጂክ ዕቅድ 5 በመቶ ብቻ ሲሆን ይህም በብሔራዊ ደረጃ አቅርቦቱ በጣም አነስተኛ መሆኑን ያመላክታል። በአጠቃላይ የኮንደም ስርጭቱ ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑት፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች፣ ለመከላከያ ሠራዊት፣ ለፖሊሶች፣ ለቀን ሰራተኞች እና ለሌሎች ለቫይረሱ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት ተሰጥቶት አልተሠራም፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት




88. በ2010 1.5 ሚሊዮን የአባላዘር በሽታ ሕሙማን ሕክምና እንደሚያገኙ፣ ሕክምና ከሚፈልጉ መካከል 94 በመቶ አገልግሎት እንደሚያገኙ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ ግን 5 በመቶ መሆኑን፣ እንዲሁም በ2000 ዓ.ም. እና በ2001 ዓ.ም. ሕክምና ያገኙት ታካሚዎች ብዛት በጽ/ቤቱ ሪፖርት ላይም እንደማይካተት፣ በጤና ተቋማትም በኩል በተጠናከረ መልኩ ሪፖርት አልመደረጉ ታውቋል፡፡

89. የመረጃ ዴስክ፣ ፀረ-ኤድስ ክለብንና ሚኒ ሚዲያ መመስረትና ማጠናከር በአንድ ት/ቤት 30,000.00 ብር ለመደገፍ በ1224 ት/ቤቶች በዕቅድ ተይዟል፡፡ ይሁን እንጂ በናሙና በመረጥናቸው የአማራ፣ የጋምቤላ ፣የትግራይ እና የኦሮሚያ ክልሎች እና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር በሚገኙ ት/ቤቶች የገንዘብ ድጋፍ አለመደረጉ፣ በክልል የኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ መከላከያ መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶችም ሆነ በክልል ትምህርት ቢሮዎች በኩል የገንዘቡ ድጋፍ ለመደረጉ መረጃ ያለመቅረቡ ታውቋል፡፡

90. በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የመለዮ ለባሾችና ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አንጻር በጽ/ቤቱ በኩል 15 የማሰልጠኛ ተቋማት እና በሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች አቅማቸዉን ለማጠናከር በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም፣ በናሙና በመረጥናቸው ክልሎች በሚገኙ የማረሚያ ቤቶች፣ በቢሮዎችና በሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች

በመስጠት ድጋፍ አለመደረጉና፣ በማረሚያ ቤቶች አካባቢ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ትኩረት ተሰጥቶት የክትትልና የግምገማ ሥራ አለመሠራቱ ተገልጿል፡፡

91. ለፖሊስ 2000 ለመከላከያ 5000 እና ለቀን ሰራተኞች 5000 በድምሩ 12,000 የመረጃ ማዕከላት በ2001-2002 ዓ.ም ለማቋቋም በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በናሙና በመረጥናቸው ክልሎች ውስጥ የመረጃ ማዕከላቱ ተቋቁመው አልተገኙም። ለበጎ ፈቃደኞች የፀረ- ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ አራማጆች ተዛማጅ ግንዛቤ መስጫ ቁሳቁሶች ማዘጋጀትና መሰራጨት በሚል በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ቁሳቁሶቹ ተዘጋጅተውና ተሰራጭተው አልተገኙም፡፡

92. ከወላጅ አልባ ህጻናት ዉስጥ ቢያንስ 10% ያህል በ2000 ዓ.ም የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ ተብሎ የታቀደ እና ሥራው መከናወኑ ታውቋል፡፡

93. ለአባላዘር በሽታዎች የሚሰጠዉ ሕክምና ዉጤታማ እንዲሆን በግልም ሆነ በመንግስት የጤና ተቋማት ለተሰማሩት (4881X2)=9762 የጤና ባለሙያዎች ተገቢዉ ስልጠና ለመስጠት በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፤ በአባለዘር በሽታ ዙሪያ በግልም ሆነ በመንግስት የጤና ተቋማት ተገቢው ስልጠና አልተሰጠም፡፡ ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ በስተቀር ሌሎቹ በናሙና የተሸፈኑት ክልሎች ከአባለዘር በሽታ ጋር የተያያዘ ሥልጠናን አስመልክቶ የገንዘብም ሆነ ሌላ ቴክኒካል ድጋፍ እንዳላገኙ ገልጸዋል፡፡

94. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው፤ የኮንደም ሥርጭትን በተመለከተ ክንውኑ ከዕቅድ ያነሰው በዕቅድ ወቅት በቂ የሆነ ግምት ስላልተሰራ ክንውኑ ማነሱን በ2003 በጀት ዓመት ግን ግኘውን በዕቅድ በመያዝ የተሻለ ለመስራት ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣ የሴት ኮንደምን በተመለከተ ተጠቃሚው አናሳ መሆኑና ዋጋው ከፍተኛ በመሆኑ የአቅርቦት እጥረት መፈጠሩን በሚቀጥሉት አመታት ግን የተጠቃሚውን ቁጥር ለመጨመር፣ ግዢ በበቂ ሁኔታ አቅርቦቱ እንዲኖር እና ግማሹ ተጠቃሚዎች ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት ክፍሎች እንዲሆኑ ለማድረግ መታቀዱን ገልጸዋል፡፡ የአባለዘር በሽታ ህሙማን አገልግሎቶቹን በግልም ሆነ በመንግስት ተቋማት ከሌሎች ህክምናዎች ጋር ተዋህዶ (Integrated) የሚሰጥ በመሆኑ ለአመዘጋገብ እና ለሪፖርት አስቸጋሪ በመሆኑ ሲሆን፣ ሥልጠናን በተመለከተም ሥልጠናው ሳይሰጥ ቀርቶ ሳይሆን ባለው የባለሙያ መቀያየር እና ያሉትም ለመሰልጠን ካላቸው ገጉት የተነሳ ነው የተጋነነው ብለዋል፡፡

95. ለመረጃ ዴስክ እና ለሚኒ ሚዲያ ማቋቋሚያ እና ማስፋፊያ የተመደበው ገንዘብ ለክልል ት/ቢሮዎች የተላለፈ መሆኑን ከየክልሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ

ጽ/ቤቶች ሪፖርት መደረጉን፣ የአፈጻጸም እና የሥልጠና መመሪያው ተዘጋጅቶ ለክልሎች የተሰራጨ ቢሆንም እርሱን መሰረት አድርገው ክልሎች ተዛማጅነት እና ክልል ተኮር የሆኑ አጋዥ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት የሚጠበቅባቸው በመሆኑ ወደፊት እንደ ትኩረት አቅጣጫ በመያዝ ከክልሎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር እንደሚሰሩበት ገልጸዋል፡፡

96. በቀበሌ ደረጃ የሚሰሩ ማናቸውም የፀረ- ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ሥራዎች ከሌሎች የጤና አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅተው በጤና ኤክስቴንሽን ማዕከልነት እንዲሰሩ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ስምምነት ላይ ስለተደረሰ የበጎ ፈቃድ መልዕክተኞችም በዚሁ መዋቅር እንዲመራ ተደርጓል ብለዋል፡፡ ወላጅ አልባ እና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑትን ሕፃናት አስመልክቶ እ.ኤ.አ በ2007 በተሰራው የሲንግል ፖይንት ኢስቲሜት በመነሳት በ2010 43% የሚሆኑት እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው በመገመቱና እነዚህን ሕጻናት በተመለከተ ከክልሎች በየሩብ አመቱ በሪፖርት መልክ የማሰባሰብ ሥራ እየተሰራ ሲሆን አሁን የሪፖርት አሰባሰቡን ለማጠናከር የማህበረሰብ መረጃ ሥርዓት (CIS) ለመዘርጋት ሥራዎች እየተሰሩ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የመረጃ ማዕከላቱ ለምን እንዳልተቋቋሙ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

97. በባለብዙ ዘርፍ ምላሽ ከ2000-2003 መርሃ ግብር ላይ በዕቅድ ተይዘው ያልተተገበሩት ሥራዎች በ2003 መጨረሻ ይደረስበታል ተብሎ የታቀደውን ውጤት እንደዳይገኝ ያደርጋል፡፡

**ለግንዛቤ ማስጨበጫ የተዘጋጁ መመሪያዎች ለመሰራጨታቸው ማረጋገጥ አለመቻሉ፣**

98. የህዝብ ንቅናቄን ለማስፈጸም የሚረዱ የአፈጻጸም መመሪያዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፤ የተዘጋጁትም በሥራ ላይ እንዲውል ለክልሎች ብሎም ለዞን እና ለወረዳ ተሰራጭተው በአገር አቀፍ ደረጃ መመሪያው ተግባራዊ ተደርጎ ንቅናቄው ወጥ በሆነ መልክ መከናወንና አፈጻጸሙ ላይ ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

99. ይሁን እንጂ በፌዴራል ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት መጋዘን ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.ገቢ የተደረጉ በቁጥር 1,500 የሕዝብ ንቅናቄ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች የተገኙ ሲሆን፣ ለኦዲቱ ጉብኝት በተደረገባቸው ክልሎች አልተገኘም፡፡

100. ስለ ጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው፣ የተለያዩ የአፈጻጸም እና የስልጠና መመሪያዎች ተዘጋጅተው እና በቦርድ እንዲጸድቁ ተደርገው፣ ለክልሎች እና ለሌሎች

ባለ ድርሻ አካላት ያሰራጩ መሆኑንና ክልሎችም በተዋረድ እንደ አስፈላጊነቱ በክልላቸው ቋንቋ በመተርጎም መጠቀም እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በአማራና በትግራይ ክልል መመሪያው እንደሌለ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት ከኃላፊዎቹ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ የላከበትን ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ሊያቀርብ ባለመቻሉ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

101. ከፍተኛ ወጪ ወጥቶበት የተዘጋጁት የሕዝብ ንቅናቄ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች ሥራ ላይ አለመዋላቸው በየደረጃው እየተሰራ ያለውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

<u>በክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች እና ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ አካላት መካከል ያለውን የተቀናጀ አሠራር ስለአለመኖሩ፣</u>

102. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ከለጋሾችና በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ አካላት ጋር የተቀናጀ የአሰራር ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ ጽ/ቤቱም ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ አካላትን ማስተባበር ይገባዋል፡፡ በተመሳሳይም በክልሎችና በሌሎች አስፈጻሚ አካላት ሥርዓቱ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

103. በአገሪቱ በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ዙሪያ የሚሰሩ አካላት በጋራ የሚያቅዱበትና የሥራ ድርርቦሽ እንዳይፈጠር የመልካም ተሞክሮ አሠራር በአብዛኛው እንዳለ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኦሮሚያ ክልል የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤት በዕቅዳቸው መሰረት ለመስራት ወደ ወረዳዎች ሲሄዱ ያለእነርሱ እውቅና በመንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ሥራው ተሰርቶ እንደሚያገኙ፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ በሚገኙ ክፍለ ከተሞች ላይም የሥራ ድግግሞሽ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር እንዳለ ተገልጿል፡፡

104. ይህም በእነዚህ ክልሎች እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በጋራ የሚያቅዱበትና አፈጻጸማቸውን የሚገመግሙበት ሥርዓት የሌለ መሆኑን ያመላክታል፡፡ አሠራሩም ካለን ውስን ሀብት አጠቃቀም አንፃር ሲታይ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>የእቅድ እና የበጀት አፈጻጸም ላይ ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ስለአለመኖሩ፣</u>

105. የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ፕሮግራሙን ስኬታማ ለማድረግ አገር አቀፍ ግልፅ የሆነ የእቅድና የበጀት አፈጻጸም፣ የክትትል፣ ቁጥጥርና ግምገማ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በተዘረጋውም ሥርዓት መሰረት በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚና ተቆጣጣሪ አካላት ሥራው በዕቅዱ መሠረት እየተከናወነና እየተፈጸመ መሆኑን በየደረጃው ሊያረጋግጡና ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

106. ይሁን እንጂ የተለያዩ የመንግስት ሴክተሮችና የተለያዩ አስፈጻሚ አካላት ለፀረ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተግባራት የተላከላቸውን ገንዘብ በወቅቱ እንደማይጠቀሙ፣ ተገቢውን ክትትል የማያደርጉ የማወራረጃ ጊዜ ገደብ ሲቃረብ ብቻ በመሯሯጥ ገንዘብ ለመጠቀም ጥረት ስለሚያደርጉ አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡ በናሙና በተመረጡ አስፈጻሚ አካላት አሠራር እንደተመለከትነው፣ የዕቅድ አፈፃፀምን ለመከታተል እና ሪፖርት ለማድረግ ወቅታዊ ክትትል እና ግምገማ አይደረግም፡፡ ነገር ግን ሊጋሽ አካላት ለግምገማ ሲመጡ በስልክ ከማሳወቅ ውጭ፣ ወጥ በሆነ መልኩ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ተግባራዊ አይደረግም፡፡ በአዲስ አበባ ጉብኝት በተደረገባቸው ክፍለ ከተሞች በ2002 በጀት ዓመት ክትትል ለማድረግ በጀት እጥረት ማጋጠሙን ገልጸዋል፡፡

107. በተለይም በጋምቤላ ክልል የኤድስ ምክር ቤት፣ አመራር ቦርድና ሪቪው ቦርድ በተጠናከረ መልኩ እየተንቀሳቀሰ አለመሆኑን እንዲሁም በየዓመቱ መጀመሪያ አጋሮቹ (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) ዕቅዶቻቸውን እንደማያሳውቁ እና የሠሩትንም ሥራ ሪፖርት እንደማያደርጉ ታውቋል፡፡

108. ለዚህም የግሎባል ፈንድ ኦዲት ሪፖርት አብዛኛው ለክልሎች የተላከው የገንዘብ አጠቃቀም በተባለው ጊዜ ውስጥ ስለማያልቅ አሳሳቢ እንደሆነ፣ በተለይም በአንዳንድ ክልሎች ሁኔታው የከፋ መሆኑ እና ክልሎች 35.2 ሚሊዮን ዶላር በ4 ወር ጊዜ ውስጥ በሥራ ላይ አውለው እንዲያወራርዱ እንዲደረግ በጽ/ቤቱ ነሐሴ 2002 ዓ.ም. ማሳሰቢያ መሰጠቱ ታውቋል፡፡

109. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው፤ ባላቸው አቅም የክትትል እና የግምገማ ሥራ እየሰሩ እንደሆነ እና የጋራ የሆነ ድጋፋዊ ጉብኝት በማድረግ ሁኔታዎችን ለመከታተል እንደሚጥሩ ገልጸዋል፡፡ ገንዘቡ በቶሎ እንዲወራረድና የተባለው በዝቅተኛ አፈጻጸም ምክንያት የፕሮጄክት ጊዜው ማራዘሚያ ተጠይቆለት የተገኘ ገንዘብ በመሆኑ ፈንዱን ላለማጣት የተደረገ ግፊት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

110. በክልል የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራም አፈጻጸምን የሚከታተልና የሚገመግም የተጠናከረ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሥራ አመራር ቦርድ እና ሪቪው ቦርድ በሁሉም ደረጃዎች (በክልል፣በዞን፣ በወረዳ) በእኩል ሁኔታ አለመዋቀር ያለውን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በሚፈለገው መልኩ እንዳይተገበር በማድረግ ለዕቅድ አፈጻጸሙ ዝቅተኛነት ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>በየመ/ቤቶቹ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ሜይንስትሪሚንግ</u>
<u>የማድረግ እንቅስቃሴን በተመለከተ</u>

111. የፌደራልና የክልል የሴክተር መ/ቤቶች ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ሜይንስትሪሚንግ በማድረግ በአመታዊ እቅዳቸዉ ዉስጥ በማካተት ተግባራዊ ማድረግ አለባቸዉ፡፡ በአመታዊ ዕቅዳቸዉ ላይ የያዙትን ዕቅድ አፈጻጸም በየሶስት ወሩ መገምገም አለባቸው፡፡ ከዓመታዊ በጀታቸውም 2% የሚሆነውን ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ መመደብ አባቸው፡፡ የዚህን እንቅስቃሴ ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ሆነ የክልል ኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ ጽ/ቤቶች አስፈላጊዉን ድጋፍ መስጠት አለባቸው ::

112. ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው:-

- በኦሮሚያ በክልል/ዞን/ወረዳ ካሉት 6920 መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ በ2002 በጀት ዓመት 2925ቱ 20% የሜንስትሪሚንግ በማድረግ ፈንድ ያቋቋሙ፣ 64% አስተባባሪ የመደቡ፣ 36% በጀት የመደቡና 42% በመቶ ብቻ ዕቅዱን በእቅዳቸው ውስጥ አካተው እንደሚንቀሳቀሱ ታውቋል፡፡ በአማራ ክልል ሜይንስትሪሚንግ ለማድረግ 3209 ሴክተሮች በ2002 ዕቅድ አዘጋጅተዋል፡፡ 2961 ኤድስ ፈንድ አቋቁመዋል፣ 3053 2% በጀት መድበዋል፡፡ የኤድስ ፈንድና የተመደበውን የ2% በጀት ማስፈፀሚያ ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡ ነገር ግን በአማራ ክልል የሴክተር መ/ቤቶች የመደቡትን 2% በጀት በአግባቡ ለታለመለት ተግባር አለመዋል ችግር መኖሩም ተገልጿል፡፡
- በጋምቤላ ክልል ደግሞ በ2002 ዓ.ም ካሉት 257 መ/ቤቶች ከመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ ሜይንስትሪሚንግ ለማድረግ 2% በጀትም አልመደቡም፣ ነገር ግን 33ቱ ወይም 13 በመቶ ተወካይ ሰው (ፎካል ፐርሰን) ሲመድቡ 13 ወይም 5 በመቶ ዕቅድ የነበራቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

- በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ሥር ካሉት 13 መ/ቤቶች በ13ቱም አስተባባሪ ተመድቧል ነገር ግን የኤድስ ፈንድ /በጀት/ የመመደብ፣ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ በሁሉም እንዳልተሰራ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የኮልፌ ቀራንዮ እና የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተሞች ያለው የሜይንስትሪሚንግ የአፈጻጸም መመሪያ ግልጽ ባለመሆኑ ለአፈጻጸም እንደተቸገሩ ገልጸዋል፡፡ ፡

113. ጉብኝት ባደረግንባቸው የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት ከጽ/ቤቱ ሜይንስትሪሚንግን አስመልክቶ የተደረገላቸው ድጋፍ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ ለአስፈጻሚ አካላት ከ2000-2002 ዓመታት በጽ/ቤቱ የተደረገ የሜይንስትሪሚንግ እና የቴክኒክ ድጋፍ መረጃ አልቀረበም፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ በሴክተር መ/ቤቶች የክትትልና ግምገማ ስርአት ዝቅተኛ ነው፡፡ በ2002 በጀት ዓመት በጠቅላላ በአገሪቱ የኤድስ ፈንድ ያቋቋሙ ተቋማት 49 በመቶ፣ አስተባባሪ የመደቡ 80 በመቶ እስከ 2% በጀት የመደቡ 55 በመቶ ዕቅድ ያላቸው 64 በመቶ ብቻ ናቸው፡፡ በሴክተር መ/ቤቶች መሪዎችና ኃላፊዎች ለጉዳዩ የሚሰጡት ክብደት አናሳ መሆኑ እና ሜይንስትሪሚንግ ለማድረግ ከኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት አስፈላጊው የቴክኒካል፣ ስልጠና እና የቁሳቁስ ድጋፍ እየተሰጠ አለመሆኑ ጽ/ቤቱ ባካሄደው የደሰሳ ጥናት ላይ ተገልጿል፡፡

114. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ስለሜይንስትሪሚንግ አፈጻጸም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ተጠይቀው አሁን ተከናወነ የሚባለው ሥራ እንደ ተወካይ ሰራተኛን መመደብ፣ በጀትም ሆነ የኤድስ ፈንድ ማቋቋም ለሥራው ጥሩ ጅምር ቢሆኑም በየደረጃው ያሉ ተቋማት ውስጥ ወጥነት ባለው ሁኔታ ለመተግበር የየተቋማቱ ኃላፊዎች ቁርጠኝነት የሚጠበቀውን አለመሆን፣ ሥራውን እንደ አንድ የተለየ ዘርፍ ስራ (የጤናው ዘርፍ ብቻ) ወይም እንደ ተደራቢ ሥራ የማየት፣ በየጊዜው የሚመደቡትም ተወካይ ሰዎችም መቀያየር ምክንያት ሥራውን በተፈለገው መንገድ ለመተግበር እንዳልተቻለ በምክንያትነት ጠቀሰዋል፡፡ ጉዳዩንም እንደ አንድ ቁልፍ ችግር በመውሰድ በአገሪቱ ፕሬዝዳንት በሚመራው የብሔራዊ የኤድስ ምክር ቤት አመራር እንደተሰጠበት ገልጸዋል፡፡ የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትል ከባለድርሻዎች ጋር በማካሄድ ለክልሎች እና በናሙና በተመረጡ የሴክተር መስሪያ ቤቶች ድጋፍ መስጠታቸውን ሌሎች ሴክተር መ/ቤቶችን ለመቀስቀስ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን መ/ቤቶች አሠራር በመገናኛ ብዙሃን እንዲተላለፍ ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

115. ይሁን እንጂ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን በመ/ቤቶች ውስጥ ሜይንስትሪሚንግ ባለመደረጉ በተለይም ሥራቸው ይበልጥ ተጋላጭ ለሚያደርጋቸው ሴክተር መ/ቤቶች ዕቅዳቸውን ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር እንዳይቃኙት አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እውቀትና ግንዛቤ አናሳ መሆንና ቁርጠኝነት አለመኖር እና የኤድስ ግብረ ኃይል በአንዳንድ የሥራ ቦታዎች መዳከም የሴክተር መ/ቤቶች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሜይንስትሪሚንግ አፈፃፀምን ዝቅተኛ አድርጎታል፡፡

116. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በየሴክተሩ በመካሄድ ላይ ባለው የልማት እንቅስቃሴና በአምራች ኃይሉ ላይ እያደረሰ ያለውን ጥፋት ለይቶ ካለመረዳት፣ የኔነት ስሜት ማጣት፣ ግልፅ የሆነ የአፈፃፀም መመሪያ ባለመኖር፣ በተለይ የከፍተኛ አመራር ላይ ያሉ ሰዎች ሜይንስትሪሚንግ ላይ የክትትል ሥርዓት አናሳ መሆን በወቅቱ ሪፖርት እንዳይቀርብ፣ የመደቡትን 2% በጀት በአግባቡ ለተለመለት አላማ እንዳይውል፣ በበላይ አካላት ትኩረት እንዳይሰጥ እና እንቅስቃሴው በእጅጉ የተገደበ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

<u>ሥልጠናዎችን በተመለከተ ተገቢው መረጃ</u>

<u>ስለአለመያዙ፣</u>

117. በኤች.አይቪ.ኤድስ ዙሪያ ስልጠና የሚሰጠው ለሚመለከታቸው ሰዎች መሆን አለበት፡፡ በሥልጠና የተሳተፉት ተሳታፊዎችን የተመለከተ መረጃም ተጠናቅሮ ሊያዝ ይገባል፡፡ ሥልጠና የሰጡ አካላትም በየደረጃው ሥልጠናውን በተመለከተ ያጠናቀሩትን መረጃ በየደረጃው እስከ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ድረስ ሊያስተላልፉና መረጃው በየሥልጠናው ዓይነት ተጠናቅሮ በአገር አቀፍ ደረጃ መያዝ አለበት፡፡

118. ጽ/ቤቱ ከግሎባል ፈንድ ካገኘው ገንዘብ ውስጥ በጽ/ቤቱ እና በክልሎች አማካኝነት ሥልጠናና ወርክሾፕ ለማዘጋጀት በ2000 ዓ.ም. ብር 51,227,448.00 (ሃምሳ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሺህ አራት መቶአርባ ስምንት ብር)፣ በ2001 ዓ.ም ብር 90,766,434.00 (ዘጠና ሚሊዮን ሰባት መቶ ስድሳ ስድስት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ አራት ብር) በጀት የተያዘ ሲሆን ለ2002 በጀት ዓመት ለሥልጠና የተመደበው በጀት ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡

119. ለሥልጠና በተመደበው ከፍተኛ ገንዘብ ምን አይነት ሥልጠና እና ለእነማን እንደተሰጠ የሚያሳይ የተጠናቀረ መረጃ የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው ክልሎችና በአዲስ አበባ

ከተማ መስተዳደር የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከ/መቆ/ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች አስፈጻሚ አካላቶች አይያዝም፡፡ በናሙና የሥራ ጉብኝት ባደረግንባቸው የጤና ተቋማት በየጊዜው ዕውቀትን የማሻሻያ (refreshment) እና የሥራ ላይ ሥልጠና እንደማይሰጣቸው ገልጸዋል፡፡

120. በተጨማሪም በጽ/ቤቱ በኩል በኤች፣አይቪ ኤድስ ዙሪያ የተሰጡ ሥልጠናዎች፣ የተሳታፊዎች ብዛት እና ለሥልጠናዎቹ የወጣው ወጪን የሚያሳይ መረጃ ተጠናቅሮ ስለመያዙ የሚያሳይ መረጃም አልቀረበም፡፡ በአጠቃላይ ምን ያህል ሠልጣኞች፣ ምን አይነት ሥልጠና መቼ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደወሰዱ የሚያሳይ ራሱን የቻለ ዳታ ቤዝ በፌዴራልም ሆነ በክልል ተዘጋጅቶ መረጃዎቹ አይያዙም፡፡

121. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በጽ/ቤቱ የተከናወኑ የሥልጠናና ወርክሾፕ የሚያስፈልገው ወጭ ዝርዝር እና የተሳታፊዎች ብዛት በገንዘቡ ወጪ በሚደረግበት ሂሳብ መዝገብ ላይ የሚመዘገብበት ሥርዓት እንዳለ ነገር ግን ለብቻው ሥልጠናን የሚመለከት መረጃ እንደማይያዝ ገልጸዋል፡፡

122. ስለሆነም የሥልጠና መረጃዎች ተጠናቅረው አለመያዛቸው፣ ምን ያህል ሥልጠና በየትኛው ርዕስ እንደተሰጠ አለመታወቁ ተመሳሳይ ሥልጠና የወሰዱ ሰዎች ድጋሚ እንዲወስዱ ከማድረጉም በላይ ለተለያየ ዓይነት ሥልጠና የወጣውን ዝርዝር ወጪ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

<u>**ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር አብረው ለሚኖሩ ዜጎች የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን በተመለከተ፣**</u>

123. ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር አብረው ለሚኖሩ ዜጎች የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ሊዘጋጅ ይገባል። የተዘጋጀውንም ደረጃ መሠረት በማድረግ የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት ሁሉ በተዘጋጀው ደረጃ መሠረት አገልግሎቱን ሊሰጡ ይገባል።

124. ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ገቢ ማስገኛም ሆነ ድጋፍና እንክብካቤ መስጫ ደረጃ በአገር አቀፍ ደረጃ አልተዘጋጀም። በአዲስ አበባ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ገቢ ማስገኛ፣ የምግብ ድጋፍ እና የድጋፍና እንክብካቤ ደረጃ ሲዘጋጅ፣ በኦሮሚያ ደግሞ የገቢ ማስገኛ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ይሁን እንጂ በአገር አቀፍ ደረጃ በፌዴራል ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት

አማካኝነት ወጥ የሆነ ገቢ ማስገኛ፣ የምግብ ድጋፍ እና ድጋፍና የእንክብካቤ አገልግሎት መስጫ ደረጃ ተዘጋጅቶ አልተሰራጨም፡፡

125. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤ ለመነሻ እንደ ስታንደርድ የሚያገለግሉ መመሪያዎች በእንግሊዘኛ ተዘጋጅተው የተሰራጩ ሲሆን የአማርኛ ትርጉማቸው ደግሞ በሕትመት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በእንግሊዘኛ ተዘጋጅቷል የተባለውም ደረጃ በኦዲቱ ወቅት አልቀረበም፡፡

126. የመመሪያው አለመኖር በሥራ ላይ ለመሰማራት የሥራ ተነሳሽነት እና ቁርጠኝነት ያላቸው ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ዜጎችን በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ለማሰማራትና ከጥገኝነት ነጻ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ወጥ በሆነ መልክ በአገሪቱ ውስጥ እንዳይካሄድ ስለሚያደርግ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

# ክፍል ሦስት፡ መደምደሚያዎች

127. ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተመደበው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ውስጥ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣

- ፈንድ ለመጠየቅ የሚቀርቡ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ከአስፈጻሚ አካላት ማመልከቻው የቀረበበት ቀን እና ቁጥር እየተሰጠው የማይመዘግብ መሆኑ፣
- የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለማጽደቅ በሚደረገዉ ሂደት ላይ በአገር ደረጃ በተቋቋሙ የዕቅድ ገምጋሚ ባለሙያዎች ከመቅረባቸዉ በፊት በቅድሚያ በመመሪያዉ መሰረት አስፈላጊዉ ሁሉ መሟላቱን የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ዩኒት ሳያረጋግጥ መቅረቡ፣
- ለአስፈጻሚ አካላት መለቀቅ የሚገባው ፈንድ በውሉ ስምምነት መሠረት በወቅቱ የማይለቀቅ መሆኑ፣ እና የሥራ ዕቅድ ሳይቀርብ ገንዘብ የሚለቀቅ መሆኑን፣
- አስፈጻሚ አካላት ከጽ/ቤቱ የወሰዱትን ፈንድ መጀመሪያ ለጠየቁት ተግባር ለምን ሊያውሉት እንዳልቻሉ እና ወደ ሌላ ሥራ መቀየር እንዳስፈለጋቸው አሳማኝ ማስረጃ ሳያቀርቡ እና የሀገር አቀፉ የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮን ፈቃድ ሳያገኙ የሥራ ለውጥ (ሪፕሮግራም) በማድረግ ፈንዱን ከተፈቀደለት ተግባር ውጭ የሚያውሉ መሆኑን፣
- ጽ/ቤቱ ከአስፈጻሚ አካላት ጋር ውል በመግባት ፈንድ ሲለቅ የተሰጣቸውን ፈንድ የሚያወራርዱበት ጊዜ ተወስኖ በውሉ ላይ የማይቀመጥ እና የተሰጠ ፈንድ ሳይወራረዱ ተጨማሪ ፈንድ የሚለቀቅላቸው መሆኑን፣
- ስለዚህ ሂሳቡን ሲያወራርዱ በመጠየቂያው ላይ የተቀመጡት ሥራዎች ላይ በተፈቀደው ገንዘብ ልክ ለመዋሉ የመከታተያ ሥርዓት አልተደረገም፡፡ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚመለከት የአፈፃፀም መመሪያ አለመዘጋጀቱ፣
- ለተጓዳኝ በሽታ መድኃኒቶች በተመደበው ገንዘብ መድኃኒቱ ያልተገዛ እና ያልተሰራጨ መሆኑ፣ የኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ዉስጥ ያለ ነፍሰጡር እናቶች ቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎት ሽፋን በጣም አነስተኛ መሆኑ፣
- በፌዴራልም ሆነ በክልል ያለው የመረጃ አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና ልውውጥ ሥርዓት ደካማ መሆኑ፣ ጽ/ቤቱ የሚጠቀምበት ጆርናል ቫውቸር ህትመት አስቀድሞ የተዘጋጀና ቅድሚያ ተከታታይ ቁጥር የተሰጠው ሳይሆን በኮምፒዩተር የታተመ መሆኑ፣

- ጽ/ቤቱ ለጤና ጥበቃ ሚንስቴር፣ በፌዴራል ደረጃ ያሉ አስፈጻሚ አካላት፣ ለክልሎች እና ለሌሎች በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ዙሪያ ለሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት የሚሰጠውን ፈንድ የሚመዘገብበት በእያንዳንዱ ተቋም ስም የተዘጋጀ ተቀጽላ ቋት (Subsidary ledger) የሌለው መሆኑ፣
- ለጤና መረጃ አያያዝ ስርዓት (HMIS) ለመዘርጋት በተመደበው ፈንድ ሥርዓቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በሚመለከተው ኃላፊዎች የወጪ ማስረጃዎች ሆኑ የማጠቃለያ ሪፖርቶች ሳይጸድቁ በሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደትክክለኛ መረጃ በመውሰድ ሂሳብ የሚወራረድ መሆኑ፣
- በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የምክር እና የምርመራ አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማት በመመሪያው (VCT guidline) ላይ የተጠቀሰውን የመረጃ መመዝገቢያ ፎርማት የማይጠቀሙ መሆኑን፣

128. በኤች.አይ.ቪ./ ኤድሰ ዙሪያ የተገኘውን ፈንድ ለተፈቀዱት ተግባራት ብቻ መዋሉን የሚያረጋግጥ እና ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፣

- የኮንዶም አቅርቦት በዕቅድ ከተያዘው በጣም አነስተኛ መሆኑ እና የሴቶች ኮንዶም ሥርጭት ደግሞ 5% ብቻ መሆኑ፣
- ለፖሊስ ሠራዊት፣ ለመከላከያ ሰራዊት እና ለቀን ሠራተኞች ተብለው የተቋቋሙ የመረጃ መዕከላት አለመኖራቸው፣
- በትምህርት ቤቶች ወስጥ ለሚኒ ሚዲያ፣ ለፀረ-ኤድስ ክበባት እና መረጃ መዕከላትን ለማቋቋም እና ለመጠናከር ሲባል የተመደበው ገንዘብ ለትምህርት ቤቶቹ ያልተሰጠ መሆኑን፣
- የህዝብ ንቅናቄ ማስፈፀሚያ መመሪያዎች ታትመው ሳይሰራጩ በጽ/ቤቱ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑን፣
- በጋምቤላ ክልል የኤድስ ምክር ቤት፣ አመራር ቦርድና ሪቪው ቦርድ በተጠናከረ መልኩ እየተንቀሳቀሰ አለመሆኑን፣
- የፌደራልና የክልል የሴክተር መ/ቤቶች ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ሜንስትሪሚንግ የማድረግ እንቅስቃሴያቸው ደካማ መሆኑ፣
- በኤች.አይቪ.ኤድስ ዙሪያ በሚሰጥ ሥልጠናን በተመለከተ የተሳተፉት ተሳታፊዎች የወሰዱት ሥልጠና እና የወጣ ወጪን የተመለከተ መረጃ ተጠናቅሮ የሚያዝበት ዳታ ቤዝ በፌደራልም ሆነ በክልል የሌለ መሆኑ፣

- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ገቢ ማስገኛም ሆነ ድጋፍና እንክብካቤ መስጫ ደረጃ በአገር አቀፍ ደረጃ አለመዘጋጀቱ፣

በጽ/ቤቱም ሆነ በሌሎች በኤች.ይ.ቪ. ኤድስ ዙሪያ የሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያደርጉትን ጥረት የሚገታ እና አገሪቱ ተጨማሪ ፈንድ ከለጋሽ ድርጅቶች ለማግኘት የምታደርገው እንቅስቃሴን አደጋ ላይ ይጥላል፡፡

129. በአጠቃላይ በአገሪቱ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጽ/ቤቱ ከሌሎች የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር በመቀናጀትና በማስተባበር በርካታ ሥራ መስራቱ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተገኘው ሀብት በአግባቡ ሥራ ላይ ካልዋለ እንዲሁም በኤች.አይ.ቪ./ ኤድሰ ዙሪያ የተገኘውን ፈንድ አጠቃቀምን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ካልተዘረጋ የተጀመረው የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች፣ በአጠቃላይ የኤች.አይ.ቪ./ ኤድስን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የተመደበውን ሀብት አጠቃቀምን ያሻሽላሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት፡

# የማሻሻያ ሀሳቦች

130. ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተመደበው የተገኘው ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣

- አስፈጻሚ አካላት ፈንድ ለማግኘት የሚያቀርቡት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ሲያቀርቡ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ገቢ የተደረገበት ቀን እና መለያ ቁጥር ተሰጥቶት በመመዝገብ ገቢ መደረግ ያለበት እና በቅድሚያ በመመሪያዉ መሰረት አስፈላጊዉ ሁሉ መሟላቱን የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ዩኒት አረጋግጦ፣ በአገር ደረጃ የተውጣጡ የዕቅድ ገምጋሚ ባለሙያዎች ቀርቦ በሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ዉስጥ መከለስ እና ውሳኔ ማግኘት አለበት፡፡
- ጽ/ቤቱ ከለጋሽ አገራት የሚያገኘውን ፈንድ መሟላት ያለበትን አስፈላጊ መስፈርት ሁሉ እያሟላ የተፈቀደውን ፈንድ ሊሰበስብና ፈንዱ ለተፈቀደላቸው አካላት በፍጥነት ለቆ ሥራ ላይ የሚውልበትን ሥርዓት ሊያጠናክር ይገባዋል፡፡
- ጽ/ቤቱ ፈንድ ከሚሰጣቸው አስፈፃሚ አካላት ጋር ውል ሲገባ ውሉ ላይ ሥራው ተጀምሮ የሚያልቅበት ቀን፣ ፈንዱን ከተፈቀደው ተግባር ውጭ ለሌላ ተግባር መዋል እንደሌለበት፣ ሂሳቡ የሚወራረድበት ቀን እና የወሰዱትን ሂሳብ ሲያወራርዱ ብቻ ቀጣይ ፈንድ የሚለቀቅ መሆኑን የሚያሳይ አንቀጽ ሊያካትት ይገባል፡፡
- በኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት የሚፈልጉትን ወገኖች ቁጥር እና ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የቫይረሱን ስርጭት የሚዳስስ ጥናት በተቀናጀ መልኩ ሊካሄድ ይገባል፡፡ የጥናቱ ውጤትም በኤች.አይቪ.ኤድስ ዙሪያ ለሚሰሩ አስፈፃሚ አካላት ሊሰራጭ ይገባል፡፡ እንደሁም ይበልጥ ተጋላጭ ላይ የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡
- የተጓዳኝ በሽታ መድኃኒቶች ግዥ የተመደበው ፈንድ ሥራ ላይ ሊውል እና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች ሁሉ የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ከቫይረሱ ነጻ የሆነ ጤናማ ትዉልድ ለማፍራት የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማጠናከር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎትን

የማስፋፋት ሥራ በአገሪቱ በሚገኙ የጤና ተቋማት ሁሉ ተግባራዊ የሚደረግበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- በጽ/ቤቱ ሆነ በአስፈጻሚ አካላት ያለው መረጃ አያያዝ እና የልውውጥ ሥርዓት ቀልጣፋና ዘመናዊ በሆነ የመረጃ ሥርዓት የሚታገዝበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተጀመሩት ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ ሥርአቶችም ተጠናቀው ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ ጽ/ቤቱ የሚጠቀምባቸው ጆርናል ቫውቸሮች ተከታታይ ቁጥር የተሰጣቸው እና አስቀድመው የታተሙ ሊሆን የሚገባ ሲሆን ፈንድ ለሚሰጣቸው እያንዳንዱ አስፈጻሚ አካላል የተቀጽላ ቋት አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡
- ለጤና መረጃ አያያዝ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተመደበው ፈንድም በአፋጣኝ ለሥርዓቱ ዝርጋታ ውሎ ሂሳቡ ሊወራረድ ይገባል፡፡
- የሚቀርቡ የወጪ ማስረጃዎች ሆኑ የማጠቃለያ ሪፖርቶች በሚመለከተው ኃላፊዎች መጽደቃቸው ሳይረጋገጥ ሂሳብ እንዳይወራረድ ለማድረግ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡
- በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክር እና የምርመራ አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማት በሙሉ በመመሪያው (VCT guidline) ላይ የተጠቀሰውን የመረጃ መመዝገቢያ ፎርማት እየተጠቀሙ ሪፖርት የሚያደርጉበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና ይህም ወጥ በሆነ መልኩ እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሥርዓቱም ሊጠናከር ይገባል፡፡

131. በኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ ዙሪያ የተገኘውን ፈንድ ለተፈቀዱት ተግባራት ብቻ መዋሉን የሚያረጋግጥ እና ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፣

- ጽ/ቤቱ ከ2000 ዓ.ም. እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ተግባራዊ ለማድረግ ያዘጋጀው በባለብዙ ዘርፍ የድርጊት ምላሽ መርሃ ግብር ላይ ከታቀዱት ሥራዎች መካከል የኮንዶም አቅርቦት በዕቅድ ከተያዘው በጣም አነስተኛ በተለይም የሴቶች ኮንዶም ሥርጭት እጅግ በጣም አነስተኛ ስለሆነ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የሥርጭቱ መጠን የሚያድግበትን መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡ በዕቅድ ተይዘው የነበረው ለፖሊስ ሠራዊት፣ ለመከላከያ ሰራዊት እና ለቀን ሠራተኞች ታስበው ነገር ግን ያልተቋቋሙ የመረጃ ማዕከላት ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ እና አስፈጻሚ አካላት ጋር በመተባበር እንዲቋቋሙ ማድረግ አለበት፡፡ በትምህርት ቤቶች ወስጥ ለሚኒ ሚዲያ፣ ለፀረ-ኤድስ ክበባት እና መረጃ መዕከላትን ለማቋቋም እና

ለመጠናከር ሲባል የተመደበው ገንዘብ ለትምህርት ቤቶቹ መድረሱንና ክበባቱ የተጠናከሩ መሆናቸውን የሚረጋገጥበት ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ታትመው በጽ/ቤቱ መጋዘን ውስጥ የሚገኙት የህዝብ ንቅናቄ ማስፈፀሚያ መመሪያዎች ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ተሰራጭተው ሥራ ላይ ሊውሉ፣ የተሰራጩትም መመሪያዎች በትክክል መሰራጨታቸውንና ለሥራ ፈጻሚዎች አካል መድረሱን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በሁሉም ክልል የአጋርነት መድረክ ቢኖር፣ በሁሉም አስፈፃሚ አካላት የቅንጅት ሥራ ቢሠራ እና የትብብር መድረኮች ቢጠናከሩ የሥራ ድግግሞሹን ከማስቀረቱም በላይ በኤች.አይ.ቪ. ዙሪያ የሚሠሩ ሥራዎችን ውጤታማ እንዲሆን ስለሚያደርግ በአገር ደረጃ ያለውን አፈጻጸም ከፍ በማድረግ በለጋሽ አካላት ሥራን መሠረት ያደረገ የፈንድ ልገሳ ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ በማድረግ አገሪቱን ይበልጥ ተጠቃሚ ስለሚያደርጋት መድረኩ ሊቋቋምና ሊጠናከር ይገባል፡፡

- በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘረጋው የእቅድ፣ የበጀት የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሊጠናከር እና ሥራውን ከሚያከናውኑት እና በየደረጃው እስከ ታች ድረስ ያሉትን አስፈፃሚ አካላት ድረስ ሊወርድ እና ወጥ የሆነ የክትትልና የግምገማ ሥርአት ሊጠናከር ይገባል፡፡

- የፌደራልና የክልል የሴክተር መ/ቤቶች ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ሜንስትሪሚንግ እንዲያደርጉ ለማድረግ ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሊያረጋግጥ እና አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ ለማሰማራት የሚረዳ እንዲሁም ድጋፍ እና እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው አገልግሎቱን ለመስጠት የሚረዳ ተዘጋጅቶ በዚህ ተግባር ላይ በተሰማሩ አካላት ሁሉ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በኤች.አይቪ.ኤድስ ዙሪያ የሚሰጥ ሥልጠናን በተመለከተ የተሳተፉት ተሳታፊዎችን የወሰዱት ሥልጠና ዓይነት እና የወጣው ወጪ መረጃ ተጠናቅሮ የሚያዝበት ዳታ ቤዝ በፌደራልም ሆነ በክልል ባሉ አስፈጻሚ አካላትም ሆነ ሥልጠናውን በሚያስተባብሩ የሚይዙበት ሁኔታ ተመቻችቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

132. በአጠቃላይ በአገሪቱ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የተገኘውን ሀብት በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል እና የተጠናከረ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ የጽ/ቤቱን፣ በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዙሪያ የሚሰሩ የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ከፍተኛ ሚና እደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ጽ/ቤቱን የማይመለከቱ ቢኖሩ ጽ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

**አባሪ 1**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

**<u>የኦዲት መስፈርት (Evaluative Criteria)</u>**

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፣ <u>የኢትዮጵያ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት</u>

| *የኦዲት ትኩረትአ ቅጣጫዎች* *Audit Issues* | የኦዲት መስፈርቶች */Evaluative Criteria/* |
|---|---|
| 1. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተገኘውን ሀብት በታቀደለት ጊዜ ለታቀደለት አላማ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ፣ | 1. ጽ/ ቤቱ በኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ ዙሪያ ለመስራት ፈንድ ለሚጠይቁ አካላት መምረጫ ግልጽ መስፈርት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 2.ጽ/ ቤቱ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ፈንድ መፍቀድ አለበት፡፡ |
| | 3. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ለሚሰሩ አስፈጻሚ ኣካላት እንዲሰጥ የተፈቀደ ፈንድ ጽ/ቤቱ በሚገባው ስምምነት መሰረት በወቅቱ መለቀቅ አለበት፡፡ |
| | 4.በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ዙሪያ ለሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት የሚመደበዉ ገንዘብ ምንጩን በመለየት በተያዘለት የጊዜ ገደብ መጠናቀቅና ለታቀደለት ተግባር መዋል አለበት፡፡ |
| | 5. ለአስፈጻሚ አካላት የተለቀቀው ፈንድ ከተፈቀደው ተግባር ውጭ ለማዋል የሥራ ለውጥ ለማድረግ (ሪፕሮግራም) ለሀገር አቀፉ የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ (CCM) ቀርቦ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡ |
| | 6.አስፈጻሚ አካላት የተሰጣቸው ፈንድ የሚወራረድበት ጊዜ በውል ስምምነቱ ውስጥ መጠቀስ አለበት፡፡ |
| | 7. አስፈጻሚ አካላትም በውሉ መሰረት ፈንዱን ማወራረድ አለባቸው፡፡ |
| | 8. ለአስፈጻሚ አካላት የተለቀቀ ሂሳብ ቢያንስ 70 % ሳይወራረድ ሌላ ተጨማሪ ፈንድ መለቀቅ የለበትም፡፡ |
| | 9. ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጋር በተያያዘ በሚገኘዉ ፈንድ የሚገዛ መድኃኒት ለጤና ተቋማት ሲሰራጭ የስርጭት ዝርዝር የሚያሳይ መግለጫ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 10. ኤች.አይ.ቪ /ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ኘሮግራም ዙሪያ ለማስፈፀሚያ የሚላከዉ ግብዓት (የህክምና ቁሳቁስ) ወደ ጤና ድርጅቶች በወቅቱ መድረሱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 11.በኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ዙሪያ አገልግሎት የሚፈልጉትን ወገኖች ቁጥር በመገመት በአገልግሎት ሰጪዎች (በአስተባባሪውና በአስፈጻሚ) በኩል ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| | 12.የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ህመምተኞች የተጓዳኝ በሽታዎች መድኃኒት (OIT) አቅርቦት ለሁሉም መዳረስ አለበት፡፡ |
| | 13.እድሜያቸዉ ከ15-49 የሆኑ አዋቂዎች የኮንዶም አጠቃቀም እ.ኤ.አ. 2010 ወደ 60% ማሳደግ አለበት፡፡ |
| | 14.በአባለዘር በሽታ ዙሪያ ህክምና ከሚፈልጉ መካከል እ.ኤ.አ. 2010 94% አገልግሎት እንዲያገኙ የተመደበው ፈንድ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 15. ለአባላዘር በሽታዎች ሥልጠና የተመደበው ገንዘብ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉ መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | 16. በአንድ ት/ቤት 30,000.00 ብር በመደገፍ በ1224 ት/ቤቶች የመረጃ |

| *የኦዲት ትኩረትአ ቅጣጫዎች*<br>*Audit Issues* | **የኦዲት መስፈርቶች** /*Evaluative Criteria*/ |
| --- | --- |
| | ዴስክ፣ ፀረ-ኤድስ ክለብንና ሚኒ ሚዲያ መመስረትና ማጠናከር አለበት:: |
| | 17. በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከል ዙሪያ እንቅስቃሴ እንዲያደረጉ የመለዮ ለባሾችና የማረሚያ ቤቶችን በቢሮዎችና በሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች ጽ/ቤቱ አቅማቸዉን ማጠናከር አለበት:: |
| | 18. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍን መከላከል አገልግሎት በአገሪቱ ውስጥ በሁሉም አካባቢ መዳረስ አለበት:: |
| | 19. ኤች. አይ. ቪ በደማቸዉ ዉስጥ ያለ ነፍሰጡር እናቶች የቫይረሱ ከእናት ወደ ፅንስ/ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎት 80 % የሚሆኑት እ.ኤ.አ. በ2010 ማግኘት አለባቸው፡፡ |
| | 20. እ.ኤ.አ. 2010 የፀረ- ኤች.አይ. ቪ/ ኤድስ ህክምና የሚያገኙ ወገኖች 100% መዳረስ አለበት፡፡ |
| | 21. በእያንዳንዱ ቀበሌ 8 የማህበረሰብ ዉይይት በየ 15 ቀናት ለ 10 ወራት መካሄድ አለበት፡፡ |
| | 22. ለበጎ ፈቃደኞች የፀረ- ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ አራማጆች ተዛማጅ ግንዛቤ መስጫ ቁሳቁሶች ማዘጋጀትና መሰራጨት አለበት:: |
| | 23. የህዝብ ንቅናቄ ማስፈፀሚያ መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለሁሉም ቀበሌዎች መሰራጨት አለበት፡፡ |
| | 24. ለፖሊስ 2000 ለመከላከያ 5000 እና ለቀን ሰራተኞች 5000 በድምሩ 12,000 የመረጃ ማዕከላት ከ2001-2002 ዓ.ም መቋቋም አለባቸው፡፡ |
| | 25. ከወላጅ አልባ ህጻናት አገልግሎቱ ከሚያስፈልጋቸው ዉስጥ ቢያንስ 10% ያህል በ2000 ዓ.ም የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ |
| | 26. ለወላጅ አልባ ህጻናት ድጋፍ የሚያገኙትን ለመመርጥ ሚረዳ ግልጽ የሆነ የመመርጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል:: |
| | 27. በእያንዳንዱ ጤና ተቋማት በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ላይ የሚሰጠዉ አገልግሎት የተሟላ መሆን አለበት:: |
| | 28. የአባላዘር በሽታ መመሪያ እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን አሳትሞ ለ 3303 የመንግሥት እና ለ1578 የግል በጠቅላላዉ ለ 4881 ተቋማት አዘጋጅቶ ማሰራጨት አለበት:: |
| | 29. ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት ተሰጥቶ የቫይረሱን ስርጭት የሚዳስስ ጥናትና የአፈፃፀም መመሪያ መኖር አለበት:: |
| | 30. በክልል ለሚገኙ ዕድሜቸዉ ከ15-49 ለሚሆን ህዝቦች 60% ቅስቀሳና ትምህርት በተለያዩ ቋንቋ ማሳተምና መሰራጨት አለበት፡፡ |
| | 31. ኤች.አይ.ቪ ኤድስን በተመለከተ የተጠናከረ መረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት በሁለም በዚህ ተግባር ላይ በተሰማሩ አካላት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል:: |
| | 32. አስፈጻሚ አካላት ለወሰዱት ፈንድ በትክክለኛ ሰነድ ላይ በመመስረት የወጪ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርት መዘጋጀት አለባቸው:: |
| | 33. በኤች.አይ.ቪ ኤድስ ዙሪያ በተከናወኑ ማንኛዉም ተግባራት ላይ በየሶስት ወሩ ሪፖርት መቅረብ አለበት:: |
| | 34. ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ዙሪያ የህብረተሰብ መረጃን ለማጠናከር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሲስተም (Internet, E-mail, web-site) መዘርጋትና ተግባራዊ መሆን አለበት:: |

| *የኦዲት ትኩረትአ ቅጣጫዎች*<br>*Audit Issues* | የኦዲት መስፈርቶች /*Evaluative Criteria/* |
|---|---|
| 2. በኤች·አይ·ቪ/ ኤድስ ዙሪያ የተገኘውን ፈንድ ለተፈቀዱት ተግባራት ብቻ መዋሉን የሚያረጋግጥ ጠንካራ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ | 35. ጽ/ቤቱ በአገሪቱ ዉስጥ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስም የሚገኝን ገንዘብ ማስተዳደር አለበት፡፡ |
| | 36. የፌዴራል ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ከለጋሾችና በኤች. አይ.ቪ /ኤድስ ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ አካላት ጋር የተቀናጀ የአሠራር ስርአት መዘርጋት አለበት፡፡ |
| | 37. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ ማንኛዉንም አካል ማስተባበር አለበት። |
| | 38. በኤች.አይ.ቪ ዙሪያ የሚሰሩ አስፈጻሚ አካላትን ያሳተፈ ስትራቴጂ ሊያዘጋጅ ይገባል። |
| | 39. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት ስትራቴጂዉን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። |
| | 40. አገር አቀፍ ግልፅ የሆነ የእቅድ፣ የበጀት፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት አለበት። |
| | 41. የተዘጋጀውን አገር አቀፍ የእቅድ፣ የበጀት፣ የግምገማና ክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት። |
| | 42. የፌደራልና የክልል የሴክተር መ/ቤቶች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሜይንስትሪሚንግ በማድረግ በአመታዊ በእቅዳቸዉ ዉስጥ በማካተት ተግባራዊ ማድረግ አለባቸዉ። |
| | 43. በአመታዊ ዕቅዳቸዉ ላይ የተያዘዉ የሜይንስትሪሚንግ ተግባር በየሶስት ወሩ መገምገም አለበት፡፡ |
| | 44. ለሴክተር መ/ቤቶች የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ አስፈላጊዉን ድጋፍ መስጠት አለበት ። |
| | 45. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለባለሙያዎች ስልጠና የሚሰጠው ለሚመለከታቸው ሰዎች መሆን አለበት። |
| | 46. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ስልጠና የወሰዱ ሰዎች በሰለጠኑበት ሙያ የሚያገለግሉበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል። |
| | 47. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው መኖሩ የታወቀ ወገኖች ህክምና በሚያቋርጡበት ወቅት ህሙማኑን የመከታተያ ስልት መኖር አለበት። |
| | 48. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ዜጎች የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ መኖር አለበት። |

<u>አባሪ 2</u>

## <u>የሀገር አቀፉ የማስተባበሪያ ዘዴ ቢሮ አባላት (Country Coordinaation Mechanism, CCM Members)</u>

- **የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር / Ministry of Health/**
- **የክርስቲያን የልማትና ተራድኦ ድርጅት /Christian Relief and Development Agency/**
- **የአለም ጤና ድርጅት / World Health Organization, WHO/**
- **የኢጣሊያን ትብብር /Italian cooperation/**
- **ከኤች.አይ.ቪ ቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ማህበራት ጥምረት /Net +/**
- **የኢትዮጵያ የእምነት ተቋማት የልማት ፎረም / Ethipoian Interfaith Fourem for Development , Dialogue and Action EIFDDA/**
- **የኢትጵያ አሠሪዎች ማህበር /Ethiopian Employer fedration/**
- **የኢትዮጵያ የሕዝብ ጤና ባለሙያዎች ማህበር /Ethiopian Public Health Association, EPHA/**
- **የተባሩት መንግስታት የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ፕሮግራም / UNAIDS/**
- **ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት /HAPCO /**
- **የኢትዮጵያ የጤና እና የምግብ ምርምር ኢንስቲቱዩት /Ethiopian Health and Nutiation Research Institute, EHNRI/**